# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 092 ታኅሣሥ 2 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ስኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





(ፎቶ ሳሙኤል ተስፋዬ)

አፈጉባኤ ታገሰ ጫፎ ኤግዚቢሽኑን ሲጎበኙ

# በመፍጠርና በመፍጠን ለዘላቂ ልማት መሥራት እንደሚገባ አፈጉባኤ ታገሰ ጫፎ አሳሰቡ

-የአቪዬሽን ኢኖቬሽን ኤክስፖ 2016 ተከፍቷል


ገጽ 4










## የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ የማስፋፊያ ፕሮጀክት ይፋ ተደረገ

- ለፕሮጀክቱ ከ35 ቢሊዮን ብር በላይ ያስፈልጋል

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ የማስፋፊያ ፕሮጀክት ይፋ ተደረገ፡፡ ለፕሮጀክቱ ግንባታ ከ35 ቢሊዮን ብር በላይ


የአፍሪካ አመራር... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ኮሚሽነር መላኩ ወልደማርያም

## ሀገራዊ ምክክሩን አካታችና አሳታፊ ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ ነው

አዲሱ ገረመው

አዳማ፡- በሀገራዊ ምክክሩ ሀገርን የማሻገር ተልዕኳችን እንዲሳካ ሂደቱን አካታችና አሳታፊ ለማድረግ ሰፊ ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ነው ሲሉ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽነር መላኩ ወልደማርያም ገለጹ፡፡


ሀገራዊ ምክክሩን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## “የተዳከመች ኢትዮጵያን መፍጠር የሚፈልጉ አካላት የሚከፍቱት የስም ማጥፋት ዘመቻ ሠራዊቱን ከዓላማው አያዘናጋውም”

- ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የተዳከመች ኢትዮጵያን መፍጠር የሚፈልጉ አካላት በሠራዊቱ ላይ የሚከፍቱት የስም ማጥፋት ዘመቻ ሠራዊቱን ከዓላማው እንደማያዘናጋው የኢፌዲሪ መከላከያ ሠራዊት ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ገለጹ፡፡

ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ከኢዜአ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ እንደገለጹት፤ በአሁኑ ወቅት አንዳንድ ኃይሎች የሠራዊቱን ስም በማጠልሸት ከዓላማው ለማዘናጋት የስም ማጥፋት ዘመቻ ከፍተዋል፡፡

ሠራዊቱ ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ የከፈቱት እነዚህ ሰዎች ምንም ጥያቄ የሌላቸው ቅጥረኛ ባንዳዎች ናቸው ያሉት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፤ ሠራዊቱ የኢትዮጵያ ሠራዊት በመሆኑ ምክንያት ሀገሪቷ የመከላከል አቅሟ እንዲዳከምና እንዲሸረሸር በማድረግ ለጥቃት ተጋላጭ የሆነች ሀገር እንድትፈጠር የሚሰሩ ኃይሎች አሉ ብለዋል፡፡

በሌላም በኩል ኢትዮጵያውያን ሆነው ሠራዊቱ ላይ ዘመቻ የከፈቱ ሰዎች ተልዕኮ ተቀብለው የሚሰሩ ናቸው ያሉት ፊልድ ማርሻሉ፤ የኢትዮጵያ ሠራዊት አሁን



ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ

ያለው ጠንካራ ሠራዊት መሆኑንና ይህንንም ጠላቶቻችን እንደሚያውቁ ጠቁመዋል፤ ስለዚህ ሠራዊቱ እንዲዳከም ስለሚፈልጉ መአት ቅጥረኛ ገዝተዋል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

“በመሆኑም ደመወዝ እየከፈሉ ሚዲያ ይሰጣሉ፤ ሠራዊቱ ላይ ዘመቻ እንዲከፈት ያደርጋሉ” ሲሉም አክለዋል፡፡


“የተዳከመች ኢትዮጵያን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








# መንፈሳዊ ሕክምና ለስጋዊ ፈውስ

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

ከዛሬ 10 ዓመታት በፊት ሥራ ለመፈለግ ከቤተሰቦቹ ተለይቶ አዲስ አበባ የገባው ወጣት ዘላለም ዋቅጅራ፣ ብቻውን ሲኖር ሳለ ለሳምንት ያህል በጠና ታሞ ከአልጋ ለመውረድ እንኳ አቅም ያጣበትን ጊዜ በሐዘን ስሜት ያስታውሳል። ከህመሜ በላይ የጎዳኝ ውሃ እንኳ የሚያቀብለኝ አጠገቤ ባለመኖሩ የተሰማኝ የብቸኝነት ስሜት ነው ይላል።

ጎረቤቶቹ "ይሔ ልጅ ምን ሆኖ ከደጅ ጠፋ ብለው አለመጠየቃቸው ከቤተሰቦቼ ናፍቆት ጋር ተዳምሮ ህመሜን አባብሶት ነበር" የሚለው ወጣት ዘላለም፣ የሚኖርበትን አካባቢ ከተላመደና ጓደኛ ካፈራ ወዲህ ግን፣ ቢያመው የሚጠራው፤ ብቸኝነት ቢሰማው ከጎኑ ሆኖ የሚያጫውተው አጥቶ እንደማያውቅ ይናገራል። ሰው ከየትኛውም ጊዜ የበለጠ ብቸኝነት የሚሰማው በህመሙ ሰዓት ነው የሚለው ወጣቱ፣ አይዞህ ባይ ሰው፣ የሚያበረታ ወዳጅ አጠገብ ሲኖር ህመም ይረሳል፤ አካልም ይበረታል በማለት ከሕይወት ልምዱ ያጋራል።

የኢትዮጵያ ወንጌላዊ አብያተ ክርስቲያናት ህብረት ፕሬዚዳንት መጋቢ ጻድቁ አብዶ፣ "ሰው አካላዊ ብቻ አይደለም፣ መንፈሳዊና ስነ ልቡናዊም ጭምር እንጂ" ይላሉ። ሰው አካሉ ሲታመም መንፈሱም ጭምር እንደሚታመም የሚናገሩት መጋቢው፣ አንድ ሰው አካላዊ ህመም ቢገጥመው ህክምናው አካላዊም መንፈሳዊም ሊሆን እንደሚገባው ይመክራሉ። እርሳቸው እንዳሉት "አይዞህ" "በርታ" "በቶሎ ትድናለህ" እና መሰል የሚያበረቱ ቃላት ለታማሚው አካላዊ ፈውስ ትልቅ ሚና አላቸው።

መንፈሳዊ ፈውስ ለአካላዊ ፈውስ መሰረት ነው ያሉት መጋቢው፣ እንደ ኢትዮጵያ ባለ በፈጣሪ በሚያምን ማኅበረሰብ መካከል ደግሞ ለሰዎች መንፈሳዊ ፈውስ የሃይማኖት አባቶች ትልቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው አጽንዖት ሰጥተው ይናገራሉ።

የታመመውን መጠየቅ፣ ያዘነውን ማጽናናት ከፈጣሪ የተሰጠ ትዕዛዝና ልንፈጽመው የሚገባን ግዴታችንም ጭምር ነው የሚሉት መጋቢ ጻዲቁ፣ የሃይማኖት አባቶች በህክምና ተቋማት ተገኝተው ታካሚዎችን ሲጎበኙ በታካሚዎች ዘንድ ትልቅ መንፈሳዊ ፈውስ እንደሚፈጠር ገልጸዋል። ብዙ ጊዜ ሰዎች ሲታመሙ ከዘመድ በቀር የሚያያቸው አለመኖሩን እንደሚታዘቡም አንስተዋል።

ፈጣሪን የምናገኘው ጠያቂ ባጡና የኛ ድጋፍ በሚያሻቸው ሰዎች ውስጥ ነው ያሉት መጋቢ ጻድቁ፣ በዙሪያችን ያሉ ድጋፍና ጠያቂ የሚሹትን በመጠየቅ፣ በማጽናናትና ከጎናቸው በመቆም ፈጣሪን እናገልግል፣ እናስደስታቸውም፤ እንዲህ ባለው መንፈሳችንን ደስ በሚያሰኝ ተግባር ለመፈጸም ምንጊዜም ትጉህ እንሁን ብለዋል።


መጋቢ ጻድቁ አብዶ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልና የሃይማኖት መምህር የተከበሩ ኡስታዝ ካሚል ሸምሱ በበኩላቸው፤ በእስልምና አስተምህሮት የታመመን መጠየቅ ከአንድ ሙስሊም የሚጠበቅ ግዴታ እንደሆነ በመጥቀስ፣ የታመመን መጠየቅ ለጠያቂው መንፈስ ትልቅ እርካታን የሚፈጥር መሆኑን ይገልጻሉ። ታማሚውም፣ አይዞህ ባይ ሲያገኝ፣ ሰዎች ቀርበው ሲጠይቁት፣ ምን ቸገረህ? ምንስ እናግዝህ? ብሎ የሚጠይቀው ሲኖር፣ ህመሙን ረስቶ ይበረታል፤ ሰላም ይሰማዋል፤ ነገን በተስፋ የሚመለከትበትን አቅምም ያገኛል ይላሉ።

እርስ በእርስ መጠያየቅ የሚያስገኘው መንፈሳዊ ፈውስ በግለሰብ ደረጃ ብቻ እንደማይወሰን ያነሱት መምህሩ፣ በማኅበረሰብ መካከል መጠያየቅና መደጋገፍ ሲጠነክር ማኅበራዊ ፈውስ እንዲመጣ፤ ማኅበራዊ ሕይወት እንዲጠነክር ያግዛልም ብለዋል።

መጠየቅና መደገፍ ያለብን የምናውቀውን ብቻ አይደለም ያሉት መምህሩ፣ በተለያዩ ትላልቅ የህክምና ተቋማትና ጠያቂ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በሚገኙባቸው ማዕከላትም በአካል በመገኘት የመጠየቅ፣ አብሮ በልቶ አጽናንቶ ህመምና ሐዘኑን የማስረሳትና የመደገፍ ልምድ ሊዳብር እንደሚገባ ይመክራሉ። ሰው በጾምና በፀሎት ወደ አምላኩ የሚቀርበውን ያህል የታመመን በመጠየቅም ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይቻላልም ብለዋል።


የተከበሩ ኡስታዝ ካሚል ሸምሱ

ብዙውን ጊዜ ሰው የሚሞተው በህመሙ ብቻ ሳይሆን ተስፋ በመቁረጥም ጭምር ነው ያሉት ኡስታዝ ካሚል፣ አሁን አሁን ብዙ ሰዎች ሊድኑ በሚችሉ በሽታዎች ትንንሽ ህክምናዎችንና ጥቂት ድጋፍ በማጣት በየቦታው ወድቀው እንደሚገኙ ይጠቅሳሉ። እርሳቸው እንደገለጹት፣ በሀገራችን በሁሉም ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ውስጥ የታመመን መጠየቅ፣ የተራበን ማብላት የታረዘን ማልበስ በፈጣሪ ዘንድ ትልቅ ዋጋን የሚያሰጥ ተግባር መሆኑ ይታመናል። ይህን በውስጣችን ያለውን እምነት ደግሞ ወደ ተግባር በመቀየር የወደቁትን ልናነሳ፤ ለመዳን የምታስፈልገውን ጥቂቷን ነገር አጥተው መነሳት ያልቻሉትን ልንጠይቅ ይገባል።

ኡስታዝ ካሚል፣ "አንድ ሰው ሲሞት ስለሱ ከማልቀስና ከማውራት፣ ሽር ጉድ ከማብዛትና ከሞተ በኋላ የማይጠቅመውን ብዙ ወጪ ከማውጣት ይልቅ በሕይወት እያለ ብንደግፈው፣ ምን ቸግሮሃል ብንለው የተሻለ ይሆናል በማለት አንድን ሰው በሕይወት እያለ እንደግፈው የመጠያየቅና የመደጋገፍ እሴታችንን እናጎልበት፤ የታመመውን መንፈስ በማደስ ለአካላዊ ፈውሱ የድርሻችንን እንወጣ ብለዋል።

ከፈጣሪ ዘንድ ዋጋ የምናገኘው ድጋፍና ጠያቂ ላጡ ሰዎች በምንሰጠው ቦታ፤ በምናደርግላቸው እንክብካቤ ነው ያሉት ደግሞ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መምህር ጥላሁን ሐምቢሳ ናቸው።


ጥላሁን ሐምቢሳ መምህር

እርሳቸው እንዳሉት፣ ሰው አካሉ ሲታመም አእምሮውም ይታወካል፤ ጭንቀት ውስጥ ይገባል። ከአካላዊ ህመም ይልቅ ሰውን የሚጎዳው መንፈሳዊ ህመሙ ወይም አእምሮው ውስጥ የሚፈጠረው ጭንቀት ነው። ብዙ ጊዜ የአእምሮ ህመምና ጭንቀት በአይን የሚታይ ባለመሆኑ ሰዎች አይረዱትም፣ ጭንቀትና ብቸኝነት እያሰቃየው ያለ ታማሚ፣ ሰው ካልደረሰለትና ችግሩን ካልተረዳው ህመሙ እየባሰ ለከፋ ችግር ሊዳርገው ይችላል። እንዲህ ያሉ ሰዎችን ቀርበን ችግራቸውን ስንካፈልና ስንጠይቃቸው በቅድሚያ የሚፈወሰው አእምሯቸው ወይም መንፈሳቸው ነው ብለዋል።

መምህር ጥላሁን፣ የሰው ልጅ ትልቁና ዋና የሆነውን መንፈሱን ለማከም ሁላችንም በየሆስፒታሉ፣ በየመርጃ ማዕከላትና በየአካባቢያችን ያሉ ድጋፍና ጠያቂ የሚሹ ሰዎችን መንፈስ እናክም፤ አጠገባቸው ሰው እንዳለ፤ ነገ ህይወት እንደሚቀጥል ተስፋ እንዲያደርጉ አቅም እንሁናቸው ብለዋል።

ሰው በሌሎች ዘንድ ሲፈለግ፣ አይዞህ ሲባል... የሚፈካ፣ ጠያቂ ሲያጣ፣ ጆሮ ሲነፈግ... የሚከስም፤ ሕልውናው በዙሪያው ባሉ ሰዎች ላይ የተንጠለጠለ ፍጥረት ነው። በተለይ ሰው ሲከፋው፣ በህመም ሲያዝ፣ አካሉ ሲደክም በሰዎች መሐል የመገኘት፤ ፍላጎቱ ያይላል። የሚያጽናና ቃል የሰውን ሥነ ልቡና ያክማል፤ መንፈስንም ያበረታልና ለሰዎች መንፈሳዊ ፈውስ በግልም እንደ ማኅበረሰብም ሚናችንን እንወጣ ሲሉም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ሚኒስቴሩ አርሶ አደሩን በቴክኖሎጂ የመደገፍ ጥረቱን አጠናክሮ ይቀጥላል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ግብርና ሚኒስቴር አርሶ አደሩን በቴክኖሎጂ ለመደገፍ የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታወቀ፡፡ የሀገር መሠረት የሆኑ አርሶ አደሮችን ሕይወት ለማሻሻልና ተገቢውን እውቅና እንዲያገኙ ለማድረግ በትብብር መሥራት እንደሚገባም አስታውቋል፡፡

የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ መለስ መኮንን(ዶ/ር) የአርሶ አደሮች ቀን አከባበርን በሚመለከት የባለድርሻ አካላት ምክክር ሲካሄድ ባስተላለፉት መልእክት እንደገለጹት፤ ግብርና የሀገራችን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ መሠረት ነው፡፡ በመሆኑም በማይመች ሁኔታ ውስጥ ሆነው የሀገር ዋልታ የሆነው ግብርና ዋና ተዋናይ የሆኑት አርሶ አደሮች ሕይወት እንዲሻሻልና ተገቢውን ክብር እንዲያገኙ መሥራት ይኖርብናል ብለዋል፡፡

ግብርና በተለያዩ ጊዜያት እንደ ሀገር ያጋጠሙን ልዩ ልዩ ችግሮች ተሸክሞ ወደፊት እያሻገረን ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ሰፊ የሥራ እድል በመፍጠር፣ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘትና አጠቃላይ ኢኮኖሚውን በመሸከም የማይተካ ሚና አለው ብለዋል፡፡

በመሆኑም በታማኝነት፣ በቅንነትና በታታሪነት ሀገራቸውን እያገለገሉ ለሚገኙት አርሶ አደሮች ተገቢውን ምስጋናና እውቅና መስጠት እንደሚገባ ጠቅሰው፤ ከተለመደው ኋላቀር የአሠራር ሥርዓት ተላቀው ሥራቸውን በቴክኖሎጂ እንዲደግፉ ለማድረግ የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡ በሁሉም መስክ ሕይወታቸው እንዲሻሻልም የሁሉንም ባለድርሻ አካላት በትብብር መሥራት ይጠይቃል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ሀገራቸውን በታማኝነትና በትጋት


የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ መለስ መኮንን(ዶ/ር)

የሚያገለግሉ አርሶ-አርብቶ አደሮችን በቅንነት ማገልገል እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

የአርሶ አደሮች ቀን መከበርም እና እሱን መነሻ በማድረግ ማመስገን፣ እውቅና መስጠትና ችግሮቻቸው መፍትሔ እንዲያገኙ ለማድረግ ትልቅ እድል ይፈጥራል ብለዋል፡፡

የምክክር መድረኩን ግብርና ሚኒስቴር፣ የአለማያ ግብርና ኮሌጅ ምሩቃን የሙያ ማህበርና አሊያንስ ፎር ሳይንስ የተባለ ድርጅት በጋራ ያዘጋጁት ሲሆን፣ የአርሶ አደሮች ቀን መቼ እንደሚሆን፣ በምን መልኩ እንደሚከበርና ሌሎችንም ተያያዥ ጉዳዮች አጥንቶ ለውሳኔ የሚያቀርብ ግብረ ኃይል ተቋቁሟል፡፡

የአርሶ አደሮች ቀን ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ለስምንት ተከታታይ ዓመታት ሲካሄድ እንደነበር የተጠቀሰ ሲሆን፣ የነበሩትን መልካም ልምዶች በመውሰድ የተስተዋሉ ክፍተቶችን በመሙላት በቀጣይነት በተሻለ መልኩ እንዲከበር እንደሚሰራ በመድረኩ ተመላክቷል፡፡

# የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ግንባታ በተያዘው በጀት ዓመት ይጠናቀቃል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ግንባታ በተያዘው በጀት ዓመት እንደሚጠናቀቅ የአዲስ አበባ ከተማ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት የኮሙኔኬሽን ዳይሬክተር ተወካይ አቶ ሲሳይ እንሴኔ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ግንባታው አሁን ላይ 74 ነጥብ 77 በመቶ ተከናውኗል፡፡ በዚህ በጀት ዓመት ለማጠናቀቅ እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው፡፡

ግንባታው በ10 ሺህ ሄክታር ላይ ከአንድ ነጥብ 339 ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ እየተከናወነ የሚገኝ ሲሆን፤ በውስጡ ዘጠኝ ፎቅ የአስተዳደር ህንጻን ጨምሮ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ፤የመማሪያ ክፍሎች ፤ የመኝታ ክፍሎች ፤ ጂምናዝየም የመሳሰሉትን ያካተተ ነው ብለዋል፡፡

በተጠቃሚ መሥሪያ ቤቱ በኩል የዲዛይን መሻሻል ሃሳብ መቅረቡ ብሎም ፕሮጀክቱ የቆየ በመሆኑ የኮንስትራክሽን ዋጋ ንረት በሥራ ተቋራጭ ድርጅት ላይ የበጀት እጥረት እና የግብአት አቅርቦት ችግር በማጋጠሙ ለግንባታው ሂደት ተግዳሮት መሆኑን አቶ ሲሳይ አስታውቀዋል፡፡

ቢሮው የመፍትሄ ውሳኔና የዋጋ ማካካሻ እንዲደረግለት ከከንቲባ ጽህፈት ቤት በማቅረብ ውሳኔ እንዲያገኝ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል፡፡ ግንባታውን በተያዘለት ጊዜ ለማጠናቀቅ በትኩረት ይሠራል ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ሥራ አመራር አካዳሚ ፕሬዚዳንት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ አሰፋ አስፈራሁ በበኩላቸው፤ የስልጠና እና የምርምር ማእከል ግንባታ ሲጠናቀቅ አካዳሚው የተሰጡትን ተልእኮዎች በብቃት ለመፈጸም የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

ተቋሙ ከተሰጡት አምስት ተልኮዎች አንዱ የሆነውን ስልጠና ዘርፍ በአገልግሎቶች የሚታዩ የአመለካከት፣ ክህሎት እና እውቀት ክፍተቶች ሊሞላ የሚችል ነው፡፡ በዚህም ከተማዋን ሊመራ የሚችል ብቁ የሆነ አመራር እና ባለሙያ ለማፍራት የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

ግንባታው ሲጠናቀቅም ስልጠናውን ከከተማው ብቻ ሳይሆን ከክልል ከተሞች ጋር በጋራ በመስራት ከተማዋን የስልጠና ማእከል ለማድረግ እና የአካዳሚውን ተደራሽነቱን ለማስፋት እንደሚረዳ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም የምርምርና የማማከር ሥራዎችን በስፋት ለመስራት ብሎም የትምህርት ዘርፉን ለመጀመር ያስችላል፡፡ በመሆኑም የተሟላ አገልግሎት በመስጠት እንደከተማ ብቻ ሳይሆን እንደሀገር ተጠቃሚ ያደርጋል ሲሉ አቶ አሰፋ አስታውቀዋል፡፡

ይህ የስልጠና እና የምርምር ማእከል ግንባታ በ2009 ዓ.ም በፌዴራል ግዢ ኤጀንሲ በወጣ ጨረታ የዮቴክ ድርጅት ጋር ውል የተያዘ ሲሆን፤ በሶስት ዓመት ለማጠናቀቅ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም መጠናቀቅ ከሚገባው ጊዜ በላይ ረዥም ጊዜ ወስዷል፡፡

በዚህም ተቋሙ በቂ የሆነ ቦታና ክፍሎች እጥረት እና በሕንፃ የኪራይ ወጪ ምክንያት ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት ተግዳሮት ሆኗል፡፡

አሁን ላይ ግንባታውን በባለቤትነት የአዲስ አበባ ከተማ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት ተረክቦ እያከናወነ ሲሆን፤ በጥሩ ሂደት ላይ ይገኛልም ብለዋል፡፡ አካዳሚ ኮሚቴ በማቋቋም የክትትል እና ድጋፍ ሥራው በጋራ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡



ፍሬህይወት ታምሩ

## የቴሌኮም ተደራሽነትን ለማስፋፋት 998 የሞባይል ጣቢያዎችን ለመገንባት እየተሠራ ነው

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- በሀገሪቱ ያለውን የቴሌኮም ተደራሽነት ለማስፋፋት በ2016 በጀት ዓመት 998 የሞባይል ጣቢያዎችን ለመገንባት ታቅዶ እየተሠራ ነው።

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ 2016 1ኛ ሩብ ዓመት አፈጻጸም በገመገመበት ወቅት ከቴሌኮም አገልግሎት ጋር ተያይዞ ለተነሱት ጥያቄዎች የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፍሬህይወት ታምሩ ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል።

በተያዘው የ2016 በጀት ዓመት 998 የሞባይል ጣቢያዎችን ለመገንባት ታቅዶ እየተሠራ ነው ያሉት ወይዘሪት ፍሬህይወት፤ 147ቱ በገጠር ቀበሌዎችና ወረዳዎች የሚገነቡ ናቸው ብለዋል።

በሩብ ዓመቱ በገጠር ቀበሌዎችና ወረዳዎች 50 የሞባይል ጣቢያ ግንባታ ተጀምሮ የ27ቱ ግንባታ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል። በዚህም 47 ወረዳዎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን መቻላቸውን ገልጸዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም ለበርካታ ዓመታት የመሰረተ ልማት ማስፋፊያዎችን መስራቱን ገልጸው፤ በተያዘው በጀት ዓመት የሚደረገውን የሞባይል ጣቢያ ማስፋፊያ ሳይጨምር በገጠር ቀበሌና ወረዳ አራት ሺህ 199 በከተማ ደግሞ ሶስት ሺህ 880 በድምሩ ስምንት ሺህ 76 የሞባይል ጣቢያዎች መኖራቸውን አስገንዝበዋል።

በገጠር ወረዳዎችና ቀበሌዎች የሚገኙት አራት ሺህ 199 የሞባይል ጣቢያዎች የ2ጂ ኔትወርክ አገልግሎት ብቻ ሲሰጡ እንደነበር አስታውሰው፤ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ አንድ ሺህ 556ቱ የ3ጂ ኔትወርክ አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ ተደርጓል ብለዋል።

ከ99 በመቶ በላይ የሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች አማራጭ የኃይል አቅርቦትን በመጠቀም የቴሌኮም አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ቢሆንም በሁሉም የገጠር ቀበሌዎችና ወረዳዎች አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ እንዳልተቻለ አስረድተዋል።

የቴሌኮም አገልግሎት ተደራሽና አካታች እንዲሆን ይሠራል ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ በሀገሪቱ እየተገነባ ያለውን የዲጅታል ኢኮኖሚ ተግባር ከግብ ለማድረስ ተቋማትና ግለሰቦች የሚያስፈልጋቸውን አገልግሎት በቀላሉ ማግኘት የሚችሉበት እድል እንዲፈጠር በትኩረት እንደሚሠራ አስረድተዋል።

አገልግሎቱን በሚፈለገው ደረጃ ተደራሽ ለማድረግ የውጭ ምንዛሬ ተግዳሮት መሆኑን ገልጸው፤ ገቢን ማሳደግና ያለውን ሀብት በአግባቡ መጠቀም ላይ ትኩረት እንደሚደረግ ገልጸዋል።

ዲጅታል ኢትዮጵያን ለመገንባት፣ የፋይናንስ አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ፣ ተቋማት በዲጅታል አገልግሎት ታግዘው ውጤታማ እና የመንግሥት አገልግሎቶች ቀልጣፋ ሆነው ለዜጎች ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን አብራርተዋል።

በዚህም ኢትዮ ቴሌኮም የገነባቸውን መሰረተ ልማቶች በመጠቀም የነዳጅ ግብይት፣ ግብር እና ሌሎች የመንግሥት አገልግሎቶች በዲጅታል የክፍያ አማራጮች መደረጋቸው በርካታ ውጤቶች አስገኝቷል ብለዋል።

እያንዳንዱ ተቋም የራሱን የዳታ ማእከል ለመገንባት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ፣ ባለሙያና አደረጃጀት እንደሚጠይቅ ገልጸው፤ ይህንን ለማስቀረት ኢትዮ ቴሌኮም የገነባው የዳታ ማዕከል ላይ ዳታቸውን በማስቀመጥ በቀላሉ ወደዲጂታል ትራንስፎርሜሽኑ መቀላቀል የሚችሉበት ወጪ ቆጣቢ መሰረተ ልማት ተገንብቶ 84 የሚሆኑ የመንግሥት ተቋማት እየተገለገሉበት ይገኛሉ ብለዋል።

ለዲጂታል ኢትዮጵያ እውን መሆን የቴሌኮም አገልግሎት ድርሻው የጎላ በመሆኑ የዳታ ማእከሉ የግል ተቋማትም የሚገለገሉበት መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል።

# ዓለም አቀፋዊ አስተሳሰብና ክህሎት ያሟላ ሠራዊት ለመገንባት እየተሠራ ነው

ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- የትምህርትን የማይተካ ሚና በመጠቀም ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ አስተሳሰብና ክህሎት ያሟላ ዘመናዊ ሠራዊት ለማፍራት እየሠራ መሆኑን በመከላከያ ትምህርት ስልጠና ዋና መምሪያ አስታወቀ።

"ጥራት ያለው አጠቃላይ ትምህርት ተደራሽ በማድረግ የፕሮፌሽናል ሠራዊት ግንባታ ሥራውን እናጠናክራለን" በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት በአዲስ አበባ ምክክር ተደርጓል።

የመከላከያ ትምህርትና ስልጠና ዋና መምሪያ ኃላፊ ሌተናል ጄነራል ይመር መኮንን በመክፈቻ ንግግራቸው እንደገለጹት፤ መምሪያው በእውቀት ብቁ የሆነ ሠራዊት መገንባት ላይ አተኩሮ እየሠራ ነው። ትምህርት የማይተካ ሚና እንዳለው በመረዳትና በመጠቀምም ዓለም አቀፋዊ ሠራዊት የማፍራት ሥራ ላይ አተኩሮ ነው፡፡

መምሪያው ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ግብዓት ብቁ የሆነ ሠራዊት ግንባታ ላይ ትኩረቱን ሰጥቶ በመሥራት ላይ እንደሚገኝ የገለጹት ሌተናል ጄነራል ይመር፤ ተቋማቸው ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎችን ማስተማር ስለመቻሉ ጠቅሰዋል፡፡

ሌተናል ጄነራል ይመር መምሪያው ተማሪዎችን አንፆና ብቁ አድርጎ ማውጣት ላይ የነበረበትን ክፍተት ለመሙላት የሄደበት ርቀት መልካም መሆኑን አመላክተው፤ያለ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎና አበርክቶ መምሪያው ብቻውን በሚያደርገው እንቅስቃሴ የትምህርትን ጥራትና ተደራሽነት ማስጠበቅ እንደማይችል ገልጸዋል፡፡

በዘመናዊ ሠራዊት ግንባታ ውስጥ ትምህርት ወሳኝ ሚና እንዳለው ይታወቃል ያሉት ሌተናል ጄነራል ይመር፤ በመሆኑም ትምህርት በየትኛውም ስፍራ ያለውን አይተኬ



ሌተናል ጄነራል ይመር መኮንን

ሚና በመገንዘብ በትምህርት የበለጸገ ሠራዊት ለማፍራት መምሪያው በርካታ ተግባራት እያከናወነ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ለሠራዊት አባላት ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት መስጠት፣ ጥናትና ምርምር በማካሄድ የመማር ማስተማር ሥራውን ማጠናከር፣ ልዩ ልዩ ስልጠናዎችን በመስጠት የታቀደና የተደራጀ አቅም ግንባታ ሥራ መሥራት፣ የተጠኑ መሰረታዊ የአሠራር ለውጥ ሥራዎችን ተግባራዊ የማድረግ ሥራ መሥራት፣ ለሠራዊቱ አባላት የተመረጡ የውጭ ቋንቋዎች ላይ ስልጠና መስጠት የመምሪያው ዋና ዋና ተግባራት ስለመሆናቸውም ኃላፊው ጠቅሰዋል፡፡

መምሪያው ለሠራዊቱ ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ላሉት አባላት የመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም እንዲሁም ከሰባተኛ ክፍል በላይ ለሆኑት አባላቱ የርቀት ትምህርት ፕሮግራምን የሚያስተምር ሲሆን፤ በእንግሊዘኛ፣ አረብኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ስዋሂሊ፣ ራሽያኛና ቻይንኛ ቋንቋዎችም ስልጠና ይሰጣል፡፡፡

በምክክር መድረኩ ላይ ጄነራል መኮንኖች፣ የመከላከያ ሠራዊት አመራሮች፣ የልዩ ልዩ ክፍል ኃላፊዎችና የተለያዩ መሥሪያ ቤት ተወካዮች ተገኝተዋል፡፡

# የጎዴ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ግንባታ 44 በመቶ ደርሷል

ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- የምእራብ ጎዴ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የመጀመሪያ ምእራፍ ግንባታ 44 በመቶ መከናወኑ የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ገለጸ። ግንባታው ሲጠናቀቅ 2 ሺህ ሄክታር መሬት ለማልማት ያስችላል።

የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት እና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ ብዙነህ ቶልቻ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ በሱማሌ ክልል ሸበሌ ዞን የሚገኘው የምእራብ ጎዴ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ግንባታ በአጠቃላይ 2 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር በሁለት ምእራፍ ይከናወናል።

የመጀመሪያ ምእራፍ ግንባታ 44 ነጥብ 47 በመቶ የተከናወነ ሲሆን በተያያዘው በጀት ዓመት ለማጠናቀቅ በማቀድ እየተሠራ እንደሆነ አስታውቀዋል።

ይህም ፕሮጀክቱ በአጠቃላይ 7 ሺህ 600 ሄክታር ማልማት የሚችል ሲሆን፤ የመጀመሪያው ምእራፍ ሲጠናቀቅ ሁለት ሺህ ሄክታር መሬት ማልማት የሚያስችል መሆኑን አቶ ብዙነህ ተናግረዋል።

ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ አራት ሺህ የሚደርሱ የአካባቢው አርሶአደር ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑን አቶ ብዙነህ ገልጸው፤ በግንባታ ሂደት ላይ ለአካባቢው ማህበረሰብ የተለያየ የሥራ እድል የሚፈጥርበት ሁኔታ አለ ብለዋል።

የምእራብ ጎዴ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ግንባታውን የሚያከናውነው የሶማሌ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን እና የጉድጓድ ቁፋሮ ኢንተርፕራይዝ ሲሆን፤ የማማከርና የቁጥጥር ሥራውን የሶማሌ ዲዛይን ቁጥጥር ኢንተርፕራይዝ መሆናቸውን ገልጸዋል።



እንደዚህ አይነት የመስኖ ፕሮጀክቶች የአካባቢውን የመስኖ ልማት ሽፋን ለማሳደግ ፤ከዝናብ ጥገኝነት በመውጣት ምርትን ለማሳደግ ብሎም ለአካባቢው ነዋሪዎች ተጨማሪ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ እና የገቢ ምንጭ በመሆን ሚና ወሳኝ አላቸው ሲሉ አቶ ብዙነህ ተናግረዋል።

የምእራብ ጎዴ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የመጀመሪያው ምእራፍ ግንባታ በመስከረም 2014 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን የሥራ ተቋራጭ እና አማካሪ የአቅም ውስንነት እና አካባቢው ለጎርፍ ተጋላጭ በመሆን የተለያዩ ጉዳት የማድረስና ሥራው እንዳይከናወን ተግዳሮት እንደሆነ አስታውቀዋል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን በቦታው ወክለው የሚሰሩ ባለሙያ በመመደብ በየእለቱ ያለውን አፈጻጸም እና ድክመቶች ሪፖርት ይከታተላል። በየደረጃው የክትትል እና ድጋፍ ሥራ ይሠራል፤ በመስሪያ ቤቱ ውሳኔ የሚፈልጉ ጉዳዮች ካሉ ውሳኔ ይሰጣል ብለዋል።

# በመፍጠርና በመፍጠን ለዘላቂ ልማት መሥራት እንደሚገባ አፈ-ጉባኤ ታገሰ ጫፎ አሳሰቡ

## -የአቪዬሽን ኢኖቬሽን ኤክስፖ 2016 ተከፍቷል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በመፍጠርና በመፍጠን የሀገሪቱን ፈጣን እድገት በማረጋገጥ ዘላቂ ልማት እንዲኖር መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ ገለጹ፡፡ የአቪዬሽን ኢኖቬሽን ኤክስፖ 2016 ትናንት በሳይንስ ሙዚየም ተከፍቷል፡፡

አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ “ፈጠራ ለአቪዬሽን ልህቀት” በሚል መሪ ሃሳብ በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀውን የአቪዬሽን ኢኖቬሽን ኤክስፖ 2016 ትናንት ሲከፍቱ እንደገለጹት፤ የፈጠራና የምርምር ሥራዎችን ተግባራዊ በማድረግ ለሀገራዊ ልማትና እድገት መሰላል አድርጎ በመጠቀም ብልጽግናን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

በኢትዮጵያ የቀጣይ ጊዜ ሀገራዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ የዘመኑን ቴክኖሎጂና ግንኙነቶችን መታጠቅ ያስፈልጋል ያሉት አፈ ጉባኤው፤ በመፍጠርና በመፍጠን የሀገሪቱን ፈጣን እድገት በማረጋገጥ ዘላቂ ልማት እንዲኖር መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የሀገሪቱን ቀጣይ ተስፋና ስኬት እውን ለማድረግ በመፍጠርና በመፍጠን መሥራት ተገቢ መሆኑን ጠቅሰው፤ ወቅቱ ፈጠራንና ፍጥነትን የሚጠይቅ በመሆኑ ዘመኑን በሚመጥን ደረጃ መሥራት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያን ቀጣይ ሀገራዊ ብልጽግና እውን ለማድረግ የአቪዬሽን ኢኖቬሽን አውደ ርዕይን ማካሄድ ወሳኝ መሆኑን የገለጹት አፈ ጉባኤው፤ አዲሱ ትውልድ በአዲስ እሳቤ ለእውቀትና ለሥራ የሚተጋ ዜጋ እንዲሆን መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በዩኒቨርሲቲዎችና ምርምር ተቋማት የምርምር ንድፈ ሃሳቦችን መሰረት በማድረግ ፈጠራዎችንና አዳዲስ ግኝቶችን መጠቀም እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ የፈጠራ ሥራዎችን ለሀገራዊ ልማትና እድገት መሰላል አድርጎ በመጠቀም ብልጽግናን ማረጋገጥ ይኖርብናል ብለዋል፡፡

እንደ ሀገር አዳዲስ አስተሳሰብን መላበስና ሁለንተናዊ ለውጥን ማምጣት ያስፈልጋል ያሉት አፈ ጉባኤው፤ በየተቋማቱ የተጀመሩ የሥራ ባህሎችን ምቹ ማድረግ እንደሚገባም አመላክተዋል፡፡

እንደ ሀገር የሥራ ፈጠራን ለማበረታታት የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ ገልጸው፤ በተለይም ጎታችና ውጤት አልባ እንቅስቃሴዎችን መግታት እንደሚገባም አሳስበዋል፡፡

መንግሥት ለወጣቶች የፈጠራ ሥራ የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቅሰው፤ ወጣቶች በፈጠራ ሥራ ታግዘው ሀገራዊ እድገትን ለማረጋገጥ ለሚደረገው ጥረት የበኩላቸውን ሊወጡ ይገባል ብለዋል።

የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስትር አለሙ ስሜ (ዶ/ር) በበኩላቸው፡-የአቪዬሽኑ ዘርፍ ሀገሪቱ የጀመረችውን የብልጽግና ጉዞ በማሳለጥ ለሁለንተናዊ እድገት የማይተካ ሚና እየተጫወተ ነው።

መንግሥት ወጣቶች ወደ ሥራ ፈጠራ ሥራዎች እንዲገቡ በማድረግ ላይ ነው ያሉት ዶክተር አለሙ፤ ዘርፉ በሀገር በቀል የፈጠራ ውጤቶች እንዲታገዝ የተዘጋጀ ኤክስፖ መሆኑንም ገልጸዋል።

ከቴክኖሎጂ ጋር የሚራመዱና የፈጠራ ክህሎት ያላቸው ወጣቶችን በብዛት ማፍራት እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ ከለውጡ በኋላ ለወጣቶች ፈጠራና ክህሎት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው መንግሥቱ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያን የአፍሪካ ዋነኛው የአቪዬሽን ማዕከል በማድረግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት እየተሠራ ነው ብለዋል።

በዘርፉ አሁን ያሉትንና መጪዎችን የአቪዬሽን ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም አቅም መገንባት እንደሚገባ ጠቅሰው፤ በተለይም የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግና በቀጣይም የአቪዬሽን ቴክኖሎጂዎች ባለቤት ለመሆን እየተሠራ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ጌታቸው ገለጻ፤ ከትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር ጋር በመሆን ብሔራዊ የአቪዬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ፍኖተ ካርታ እየተዘጋጀ ነው።

የኤክስፖው አላማ በራሳቸው ተነሳሽነት በአቪዬሽን መስክ በፈጠራ ሥራ የተሰማሩ ወጣቶችን ማበረታት ሲሆን፤ በተለይም በዘርፉ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን እንዲስፋፋ ማድረግ ላይ ያተኮረ ነው ብለዋል።

በአውደ ርዕዩ 95 ወጣቶች በጋራና በተናጠል 90 የፈጠራ ሥራ ውጤቶቻቸውን እንደሚያቀርቡ ጠቅሰው፤ 34 የግልና የመንግሥት ተቋማትም በዘርፉ እያከናወኑ ያሉትን የፈጠራ ሥራዎች ማቅረባቸውን ገልጸዋል።

ኤክስፖው እስከ ታኅሳስ ስድስት የሚቆይ ሲሆን፤ የአቪዬሽን ባለስልጣን ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በመሆን ያዘጋጀው የፎቶ ግራፍ አውደ ርዕይም ለእይታ ቀርቧል።

# ሀገራዊ ምክክሩን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ኮሚሽነሩ ትናንት የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካሪ ኮሚቴ አውደ ጥናት በአዳማ በተካሄደበት መደረክ እንደገለጹት፤ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የተጣለበትን ታላቅ ሀገራዊ ኃላፊነት ለመወጣት በርካታ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል። ኮሚሽኑ ተልዕኮውን ለማሳካት የተሳታፊ ልየታን ጨምሮ ሂደቱን አካታችና አሳታፊ ለማድረግ በመላው ሀገሪቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ ነው።

ኮሚሽነሩ፤ "በኢትዮጵያ በተለያዩ የሃሳብ መሪዎች፣ ፖለቲከኞችና የማኅበረሰብ መሪዎች መካከል መሰረታዊ ሀገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ለሚታዩ የሃሳብ ልዩነቶች መሰረታዊ የሆኑ ምክንያቶችን ከምንጫቸው በመለየት፤ ጥልቅ ምክክር እንዲደረግባቸው በማድረግ፤ መግባባት በመፍጠር፤ ሀገርን የማሻገር ተልዕኳችን እንዲሳካ ሂደቱን አካታችና አሳታፊ ለማድረግ ሰፊ ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ነው" ብለዋል።

አለመግባባትን በምክክር ወደ መግባባት መቀየር አለብን በሚል እሳቤ ኮሚሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የትውልዱን አደራ ለመወጣት ቃልኪዳን ገብቶ ሥራውን እያስኬደ ይገኛል ነው ያሉት።

በመርህ ደረጃ አካታችነት ትልቁን ቦታ የያዘ ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፣ በምክክር ሂደቱ ሁሉንም ዜጋ አካታች ለማድረግ የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ወደ ሥራ እንደተገባ አመልክተዋል።

እስካሁን ባለው ሥራም በድሬዳዋ፣ በሀረሪ፣ በሲዳማ፣ በደቡብ ምእራብ፣ በጋምቤላ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ የተሳታፊዎች ልየታ መከናወኑን ገልጸዋል። በሌሎች አካባቢዎችም የተሳታፊዎችና ተባባሪ አካላት ተሳትፎ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

ከተለያዩ አካላት ጋር ከሚደረገው የተሳታፊ ልየታ ሥራና፣ ከተባባሪ አካላት መረጣ ባሻገር፤ የምክክር ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆንና የሚደረስባቸው መግባባቶችም በተሟላ ሁኔታ እንዲፈጸሙ ሁነኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው በማመን የአማካሪ ኮሚቴ አባላትን በመሰየም ወደ ሥራ እንዲገቡ መደረጉን ኮሚሽነሩ ጠቅሰዋል።

የአማካሪ ኮሚቴው አባላት ከመላው ኢትዮጵያ በልዩ ልዩ መስኮች ሰፊ ተቀባይነት ያላቸውና በሙያቸው የተመሰከረላቸው ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ገልጸው፣ ኮሚቴው የተሳካ ሀገራዊ ምክክር ለማድረግ በማማከር ሂደት ውስጥ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ተናግረዋል።

ኮሚቴው ኮሚሽኑን በማማከር ረገድ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት የሚረዳ የተግባር እቅድ በማዘጋጀት እስካሁን ሲሠራ የነበረውን አጠናክሮ እንዲቀጥልም አስገንዝበዋል።

ትናንት በአዳማ ከተማ የተጀመረው የአማካሪ ኮሚቴ አውደ ጥናት ሀገራዊ ምክክሩ ላይ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችና መፍትሄዎች እንዲሁም የአማካሪ ኮሚቴ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችና ሌሎች ግንዛቤ ተኮር ውይይቶች የተካሄደበት ነው።

# “የተዳከመች ኢትዮጵያን መፍጠር...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሀገር ቤት የኛ የሚሏቸው ታጣቂዎችን በመታገል ልክ በማስገባት ፍላጎታቸው እንዳይሳካ በማድረግ በደምብ የሰራው መከላከያ ነው ያሉት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፤ መከላከያ እነሱ የሚፈልጉትን በትጥቅ ትግልም በሰላማዊ ሰልፍም በሌላም አድርገው ሀገር ለማፍረስ፤ ለማበጣበጥ፤ የእርስ በርስ ጦርነት ለመፍጠር የሚያደርጉትን ነገር የመከተው መከላከያ ነው ብለዋል፡፡

የኛን ፍላጎት እንዳይሳካ ያደረገው ብለው ጠንካራ ጎን ሲፈልጉ ጠንካራ ጎኑ መከላከያ ነው ያሉት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፤ እኛ ደግሞ ተልዕኮ አለን፤ ተልዕኮው ከውጪም ይምጣ ከውስጥ፤ በኃይል የሀገሪቷን ሥርዓተ መንግሥት፣ ሕገ መንግሥት ገርስሶ እኔ ነኝ ጉልበተኛ ብሎ በግድ በጠመንጃ ሊጭን የመጣን ኃይል በሙሉ እንዋጋለን ብለዋል፡፡

“ሠራዊቱ ተበትኗል፣በጄነራል ተጣልቷል፤ ጀነራል እገሌ ተቀቷል፤ የቁም እስረኛ ሆኗል “የሚለው ምኞት አይከለከልም ያሉት ፊልድ ማርሻሉ፤ መከላከያ በጠንካራ አለት ላይ የተገነባ ነው፤ ፍርክስክስ የሚል አጀንዳ በመጣ ቁጥር የሚጭበረበር፣ የሚርበተበት ተቋም አይደለም ብለዋል፡፡

ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ እንደገለጹት፤ መከላከያ በጠንካራ መሠረት የተገነባ በራሱ አስተምህሮ፣ሥነ ሥርዓት የተገነባ ነው፡፡ ዓላማውን ፣ ለምን እንደሚዋጋና ማንን እንደሚዋጋ የሚያውቅ መንደርተኝነት የሌለው ኢትዮጵያዊነትን የተላበሰና ኢትዮጵያን የመጠበቅ ተልዕኮን የወሰደ ነው፡፡

የመከላከያ ሠራዊት ተልዕኮ የሀገሪቷን ሉዓላዊነት መጠበቅ ነው ያሉት ፊልድ ማርሻሉ፤ የሚጠብቀውም ጠረፍ አጥሮ፣ ምሽግ፣ ሰልፍ ሰርቶ አይደለም፤ መከላከያ ሠራዊት የሀገሩን ሉዓላዊነት የሚጠብቀው ራሱ እየገነባ፣ እየሰለጠነ፣ እየታጠቀ፣ አቅሙን እያሳደገና እየተደራጀ ነው ሲሉም ገልጸዋል፡፡

ሌላኛው መከላከያ ሠራዊቱ ከፖሊስ አቅም በላይ የሆነ እና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመጣል የመጣ ማንኛውንም የሀገር ውስጥ ኃይል መቆጣጠር እንዳለበት ተልዕኮ ተሰጥቶታል ብለዋል፡፡

# የአፍሪካ አመራር...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እንደሚያስፈልግም ተጠቁሟል።።

የአካዳሚውን የሪፎርም፣ የማስፋፋትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ በተመለከተ ለአፍሪካ፣ ለእስያ፣ ለአውሮፓ እና ለተለያዩ ሀገራት አምባሳደሮች ትናንት ገለፃ ተደርጓል።

የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ርዕሰ አካዳሚ አቶ ዛዲግ አብርሃ በወቅቱ እንደገለጹት፤ አሁን ያለው የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ጥራት ያለው ቢሆንም ለኢትዮጵያና ለአህጉሩ አመራር ልማት በቂ አይደለም። የአካዳሚውንም ራዕይ ለማስፈጸም የሚያስችል መሠረተ-ልማት ማስፋት አስፈላጊ በመሆኑ የሪፎርም፣ የማስፋፋትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ ተዘጋጅቷል።

በዚህም ለአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ማስፋፊያ ግንባታ ከ35 ቢሊዮን ብር በላይ ያስፈልጋል ያሉት አቶ ዛዲግ፤ ይህ የመሰረተ ልማት ግንባታ ፍላጎት የሚሟላው በባለሀብቶች፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት እንዲሁም በውጭ ሀገር በጎ ፍቃደኞች ተሳትፎ እንደሆነ ገልጸዋል።

በማስፋፊያ ፕሮጀክቱ ከሚሰሩ መሠረተ ልማቶች መካከል አምስት ሺህ ሰው በአንድ ጊዜ ማስተናገድ የሚችል የተሟላ የኮንፈረንስ አዳራሽ፣ አምስት ሺህ



ሰው የሚይዝ ዶርሚተሪ፤ ከ500 እስከ ሁለት ሺህ 500 ሰው የሚይዙ መሰብሰቢያ አዳራሾች ይገኛሉ ነው ያሉት አቶ ዛዲግ።

ምግብ ማዘጋጃዎችና ካፊቴሪያዎች፤ የከተማ ግብርና ማዕከልና ማቀነባበሪያ፣ የጎልፍ መጫወቻ ሜዳና መዋኛ ገንዳን ጨምሮ ሁለገብ የስፖርት ማዘውተሪያ በማስፋፊያ ፕሮጀክቱ እንደሚካተት አቶ ዛዲግ ገልጸው፤ በማስፋፊያ ፕሮጀክቱ አፍሪካን የሚመጥኑ የትምህርት ፕሮግራሞችና የአመራር ክህሎቶች እንደተካተቱ ገልጸዋል።

አካዳሚው የአፍሪካውያን በመሆኑ ውጫዊ ገጽታው፣ በውስጡ የሚሰጡ ስልጠናዎችና ሌሎችም ተግባራት አፍሪካውያንን መሰረት ያደረጉ እንደሚሆንም ተናግረዋል።

እንደ አቶ ዛዲግ ገለፃ፤ ኢትዮጵያ አብዛኞዎቹ የአፍሪካ ሀገራት በቅኝ ግዛት ተይዘው በነበሩበት ወቅት ለነፃነታቸው በርካታ ሥራዎችን ሠርታለች። ዛሬም ከድህነት ለመውጣት የምታደርገው ጥረት አፍሪካውያንን መሰረት ያደረገ ነው።

ይህንን ለማድረግ የአህጉሪቱ መሪዎችን አቅም ማሳደግ ተገቢ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ለዚህም በኢትዮጵያ የሚገኘው የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ጉልህ ሚና አለው ብለዋል።

አካዳሚውን በሀገር ደረጃ መስራት ይቻላል። ነገር ግን ኢትዮጵያ የአፍሪካውያን የነፃነት አርማ መሆኗ ተጠናክሮ እንዲቀጥል አካዳሚው አህጉራዊ እንዲሆን ተደርጎ ተቀርጿል ያሉት አቶ ዛዲግ፤ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ 13 ፕሮግራሞች ያሉት የሪፎርም፣ የማስፋፋትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ ተዘጋጅቷል ብለዋል።

አቶ ዛዲግ አብርሃ፤ አካዳሚው ባለፉት ሁለት ዓመታት ያከናወናቸውንና የሠራቸውን ሥራዎች እንዲሁም በቀጣይ ሊሠራ ያሰበውን በተመለከተ መቀመጫቸውን አዲስ አበባ ላደረጉ የአፍሪካ፣ የእስያ እና የአውሮፓ ሀገራት አምባሳደሮች ገለፃ አድርገዋል።

በኢትዮጵያ የሩሲያ አምባሳደር ኤፍጌኒ ተረክህን በበኩላቸው፤ የዓለም መንግሥታት ሀገራቸውን በእውቀትና በጥበብ መምራት ይፈልጋሉ። አብዛኛዎቹ የሀገራት መሪዎችም ከዩኒቨርሲቲና ከሌሎች ዘርፎች የወጡ በመሆናቸው ሀገርን የማስተዳደር እውቀት ይኖራቸዋል ብለዋል።

አህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ የአመራር አካዳሚ ተምረው ቢወጡ ደግሞ የተሻለ ክህሎት፣ ጥበብና እውቀት ይኖራቸዋል ብለዋል።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚን ለማስፋፋት ያቀደችው ፕሮጀክት በእጅጉ የሚደነቅና ሊበረታታ የሚገባው ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ ከአካዳሚው የሚወጡ አመራሮችም በምርምር፣ በቲንክ ታንክና በማማከር አገልግሎት እንዲሁም የሕዝብ ፍላጎትን ማሟላት የሚያስችል ሃሳብና ሥራ እንደሚሰሩ አልጠራጠርም ብለዋል።

አሁን ያለው አካዳሚ በ50 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን፤ በውስጡም ዘመናዊ አዳራሾችንና አገልግሎት ሰጪ ህንጻዎችን ያካተተ ነው።። ይህንንም አምባሳደሮቹ ተዘዋውረው ጎብኝተዋል። በመጨረሻም ሁሉም አምባሳደሮች የችግኝ ተከላ አከናውነዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኤክስፖው የኢትዮጵያን የአቬዬሽን ታሪክና ልክ ለመዘከር መልካም አጋጣሚ ነው

የአቬዬሽን ኢንዱስትሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ በኢኖቬሽን ከፍተኛ እመርታ እያሳዩ ከሚገኙ ዘርፎች መካከል በዋነኝነት ተጠቃሽ ነው። ኢንዱስትሪው የአየር ትራንስፖርት አሁን ላለበት ሁለንተናዊ እድገት ትልቁ ባለውለታ ነው። በቀጣይ ለሚኖረው እድገትም ያለ አቬዬሽን የሚኖረው እገዛ የትየለሌ ነው።

በሀገር ውስጥ ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎቶች ያለ ችግር /ከአደጋ ነጻ በሆነ መንገድ / እንዲከናወኑ ፣ በቴክኖሎጂ ከመዘመን ጀምሮ ዓለም አቀፍ ሥርዓቶችን በማበጀት፤ ሥርዓቶቹ የሚገዙባቸውን ሕጎችና መመሪያዎች በማጽደቅ እና በማስፈጸም የሚታወቅ ነው።

ደረጃቸውን የጠበቁ ኤርፖርቶች መገንባታቸውን፤ ዘመኑ ባፈራቸው ቴክኖሎጂዎች ማዘመናቸውን ፤ ዘርፉ ለሚተዳደርባቸው ዓለም አቀፍ ሥርዓቶች ተገዥ መሆናቸውን በመቆጣጠር የአየር ትራንስፖርት ዘርፉ ደህንነቱን የተጠበቀና አስተማማኝ እንዲሆን ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራ ነው።

ከዚህም ባለፈ የአንድን ሀገር ሉአላዊ የአየር ግዛት ከየትኛውም ሉአላዊነትን ከሚፈታተን ስጋት ነጻ መሆኑን በመከታተል እና በማረጋገጥ ሂደት ከሌሎች የሀገር ደህንነት ተቋማት ጋር በመሆን የሚያበረክተው አስተዋጽኦ መተኪያ የሌለው ነው።

ኢትዮጵያ የቀድሞውን “ሲቪል አቪዬሽን” የአሁኑን የኢትዮጵያ ሲቪል አቬዬሽን ባለስልጣን በ1944 ዓ.ም አቋቁሞና በዚሁ ዓመትም የዓለም አቀፉን የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ስምምነት ፈርማ ለዘርፉ እድገት የበኩሏን ሚና ተወጥታለች፤ እየተወጣችም ትገኛለች።

በኢትዮጵያ የአየር ትራንስፖርት አሁን ላለበት የላቀ ደረጃ መድረስ ሲቪል አቪዬሽኑ ተጠቃሽ ባለውለታ ነው። ኤርፖርቶችን ከመገንባት ጀምሮ ዘመኑን የሚዋጁ ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ሀገሪቱ በዘርፉ በአለም አቀፍ ደረጃ አንቱታን እንድታተርፍ አስችሏል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ሀገርን በማስጠራት የሀገር ኩራት ከሆነው የኢትዮጵያ አየርመንገድ በስተጀርባ ገዝፎ የሚገኙ፤ አየር መንገዱ በሀገር ውስጥ ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች አስተማማኝ እና ተመራጭ እንዲሆኑ ከፍ ያለ ሚናን የተጫወተ በመሆኑ ምስጋናም የሚገባው የሀገር ኩራት የሆነ ተቋም ነው።

የአየር ትራንስፖርት በመላው ሀገሪቱ እንዲስፋፋ ኤርፖርቶችን ከመገንባት ጀምሮ ፤የኤርፖርት መሰረተ ልማቶችን በማሟላት እንደ ሀገር አሁን ለደረስንበት የአየር ትራንስፖርት እድገት በየዘመኑ አስፈላጊውን የአዋጅና የአደረጃጀት ማሻሻያዎችን ጭምር በማድረግ በኃላፊነት መንፈስ ሲንቀሳቀስ የነበረና አሁን በተሻለ መነቃቃት በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ተቋም ነው።

እንደ አገር የመጀመሪያው የአቪዬሽን ትምህርት ቤት ከተከፈተበት 1951 ዓ.ም ጀምሮ ተቋሙ ከሀገር ውስጥ ባለፈ፤ ለአፍሪካውያን ወንድሞቻችን ሙያዊ ስልጠናዎችን በመስጠት፤ የአየር ትራንስፖርት በአፍሪካ የተሻለ እድገት እንዲኖረው ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት ላይ ይገኛል፤ በዚህም በብዙዎች ዘንድ እውቅናና ከበሬታን ማትረፈ ችላል።

የሀገሪቱን ሉአላዊ የአየር ግዛት ለ24 ሰአታት በመጠበቅ፤ በሀገሪቱ የአየር ግዛት ውስጥ የሚደረጉ በረራዎችን ከመቆጣጠር ጀምሮ፤ ሉአላዊነትን የሚፈታተኑ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው አካላት በማስተላለፍ ለሀገር ሉአላዊነት መከበርም ሌት ተቀን የሚተጋ ተቋም ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃም ሀገሪቱ በአየር ትራንስፖርት ዘርፍ ሊኖራት የሚችለውን ተሰሚነት በማስጠበቅ ፤እንደ ሀገር ማግኘት የሚገባትን ጥቅማ ጥቅሞች በማስከበር ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሀገርና ሕዝብን ወክሎ የሚንቀሳቀስ ተቋም ነው። በቀጣይም የአየር ትራንስፖርቱ ለሚኖረው እድገት ዋነኝ ባለድርሻ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

በትናንትናው እለት በሳይንስ ሙዚየም የተከፈተውና የዘርፉን ተዋንያን ሥራዎች የሚያስቃኘው ኤክስፖ የዚህን የሀገር ባለውለታ ተቋም ሀገራዊ አበርክቶዎች ለማሳየት መልካም አጋጣሚ ነው።

ኤክስፖው በሀገሪቱ የአየር ትራንስፖርት ታሪክ ውስጥ የነበረውን እና አሁንም ያለውን ስፍራ በተጨባጭ ማሳየት ያስቻለ፤ ዜጎች ስለተቋሙ የተሻለ ግንዛቤ ኖሯቸው ለተቋሙ ተገቢውን ከበሬታ እንዲሰጡት የሚያስችልም ነው ። በተቋሙ ውስጥ ያለፉ አንቱታ ያተረፉ ባለሙያዎችን አውቆ ለመዘከርም እድል የሚሰጥ ታሪካዊ አጋጣሚ ነው።

**አዲስ ዘመን**
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።።

## የውጭ ምንዛሪን ሀገርና ሕዝብን በሚጠቅም ተግባር ላይ ለማዋል

ስምስም መንግሥቱ

ኢኮኖሚዋ በግብርና ላይ ለተመሠረተ ሀገር የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ምን ማለት እንደሆነ ለቀባሪው ማርዳት ይሆንብኛል:: የዛሬ ዋነኛ አጀንዳዬ የውጭ ምንዛሪ አስፈላጊነትን ሳይሆን፤ የውጭ ምንዛሪ አግባብ ላለው ነገር እየዋለ ነው ወይ የሚለውን ለማንሳት ነው::

ምንም እንኳን የሀገራችን የንግድ ሁኔታ በሰበብ የተሞላ ቢሆንም የዶላሩ እጥረት እውነትነት እንዳለው አይካድም:: ዛሬ ገበያው ላይ ለትልቁም ለትንሹም ዕቃ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦትን እንደምክንያት ማቅረብ እየተለመደ ነው:: የዶላር ጉዳይ የቆየውን የኢትዮጵያውያንን ተከራክሮና ተደራድሮ የመገበያየት ተሞክሮንም እያስቀረ ነው::

ነጋዴዎች አስቀድመው የዶላር አቅርቦት ችግርን በማንሳት አፍ ያስይዛሉ:: አብዛኞቹ ነጋዴዎች የዶላር እጥረትን የገበያ ማሳመኛ አድርገው እየተጠቀሙበት ነው:: በሀኪም የታዘዘላቸውን መድኃኒት ከብዙ ፍለጋ በኋላ ካገኙ ዋጋው የሚቀመስ አይሆንም ለዚህም ምክንያቱ ተመሳሳይ ነው።

እንደ ስኳርና ደም ብዛት ያለባቸው የማይቋረጥ መድኃኒት የሚወስዱ ህሙማን እየተቸገሩ፣ ለግብርናው የሚውል የአፈር ማዳበሪያና ተያያዥ ግብአቶች ግዥ ለመፈጸም ተግዳሮት ሆኖ ገበሬው እየተጨነቀ፣ በመለዋወጫ እቃ አቅርቦት ችግር አምራች ኢንዱስትሪዎች የሥራ ማሽኖቻቸውን መጠገን ባለመቻላቸው ሥራቸው እየተስተጓጎለ፣ አቅርቦትና ፍላጎትን ለማጣጣም የሚያስችል ሥራ ለመሥራት እንደሀገር ፈተና በሆነበት በዚህ ወቅት የውጭ ምንዛሪ ለእነዚህ አስፈላጊ ለሆኑ ነገሮች ሳይሆን፤ አንገብጋቢ ላልሆኑ ነገሮች ግዥ ሲውል እንታዘባለን::

መንግሥት በተለያዩ ጊዜያት ዜጎች በውጪ ምንዛሬ አጠቃቀም ዙሪያ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ከማድረግ ጀምሮ በተለያዩ ሸቀጦች ላይ ፣የዶላር ማእቀብ ቢጥልም፣አሁንም በተፈቀዱ የተለያዩ አማራጮች የውጪ ምንዛሪ መሰረታዊ ለሆኑ ሸቀጦች ከመዋል ይልቅ፣ለመዋቢያ (ኮስሞቲክስ) በስፋት ሲውል እየተስተዋለ ነው።

የቦንዳ ልብስ የሚባለውን ልባሽ ጨርቅ ጨምሮ፣ አርቲፊሻል ፀጉር(ሂማን ሄር) እና የውበት መጠበቂያ(ሜካፕ) በውጭ ምንዛሪ ተገዝተው በስፋት ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው ፤ በየመንደሩ ባሉ የውበት ማስዋቢያ እና የቦንዳ ጨርቆች መሸጫ ሱቆች ለዓይን ሞልቶ ማየት የተለመደ ነው ::

በተለይ ደግሞ አሁን ላይ በመዲናችን አዲስ አበባ የከተማ ሴቶች ያለሜካፕ እንዳትታዩ የተባሉ ይመስል ከወጣት እስከ አዋቂ እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሁሉ በስፋት እየተጠቀሙ ይገኛሉ:: ቀደም ሲል ሴቶች የበለጠ አምረውና ደምቀው ለመታየት ጥረት ሲያደርጉ የሚስተዋሉት በሰርግ እና የተለየ ጥሪ ሲኖራቸው ነበር::

ለመዋቢያ የሚጠቀሙት ግብአትም እንዲህ እንዳሁኑ ከውጭ የተቀዳ ባህልን የተከተለና በውድ ዋጋም የሚገዛ አልነበረም:: አሁን ላይ ግን ለየት ብሎ የመታየቱ ሁኔታ የዘወትር እየሆነ ፤ የሚዋቡበትም ግብአት ሙሉ ለሙሉ ከውጭ በዶላር ተገዝቶ የሚመጣ ነው::

የፊት ቆዳን ለማሳመር ወይንም ሜካፕ ለመደረግ የተለያዩ ግብአቶች ያስፈልጋሉ:: የፊት ቆዳ ካማረ በኋላ የዓይን ኩል፣አርቲፊሻል ሽፋሽፍት፣የከንፈር ቀለም፣አርቲፊሻል ጥፍርና የጥፍር ቀለም ተጨማሪ መዋቢያዎች ናቸው:: መዋቢያው ደረጃ ስላለው የሚጠየቀው ክፍያም እንደደረጃው የተለያየ ነው:: ክፍያውም የሚቀመስ አይደለም::

ግብአቱ ከውጭ በዶላር ተገዝቶ እንደሚገባና በብዙ ችግር እንደሚያስገቡት አስቀድመው ስለሚነግርዎት ያለዎት አማራጭ አገልግሎት ሰጪዎቹ በሚሏችሁ ዋጋ መጠቀም ነው:: አንዳንዶቹም ግብአታቸው ጥራት እንዳለውና ከሌሎች የተሻለ እንደሆነ አግባብተው ስለሚነግሯችሁ የሚጠይቁትን ከፍ ያለ ክፍያ ለመክፈል ይገደዳሉ::

የሚገርመው ግን ተጠቃሚው እነዚህን ሁሉ አውቆ ነው እየተጠቀመ ያለው:: ፍላጎት መኖሩን የሚያሳየው ደግሞ እንደአሸን በፈላው መሸቀጫ ውስጥ እንደፈጣን ምግብ (ፋስትፉድ) ሁሉ ፈጣን የመዋቢያ አገልግሎት

**ጤናማ የአመጋገብ ሥርዓትን መከተል ከተቻለ ውበት ይጠበቃል:: የጤና ችግር ሲያጋጥም ደግሞ ታክሞ ለበሽታው የሚሆን መድኃኒት ያስፈልጋል**

የሚሰጡ መኖራቸው ነው:: ወደ አንዱ መሸቀጫ ጎራ ብሎ በስሱ ቀባ ቀባ ብለው እስከ አንድሺ ብር ከፍለው ይወጣሉ:: በማሳመር(ሜካፕ) ሥራ ላይ የተሰማሩት እንደሚሉት ጥራት ላለው ሥራ ከፍ ያለ ክፍያ ይጠይቃሉ:: የሜካፕ ማሰልጠኛዎችም እንዲሁ በመዲናዋ መስፋታቸውን በሶሻል ሚዲያና በማስታወቂያዎች ከምንሰማውና ከምናየው መረዳት እንችላለን::

አንዳንድ የስልጠና ተቋማትም እራሳቸውን ዓለምአቀፍ (ኢንተርናሽናል) ብለው በመሰየማቸው ለስልጠና የሚጠይቁት ክፍያም ከፍ ያለ ነው:: ለአንድ ወር ለአንድ ሰልጣኝ እስከ 65ሺ ብር በማስከፈል ስልጠና የሚሰጡ ማሰልጠኛዎች እዚሁ መዲናችን ውስጥ ይገኛሉ:: ስልጠናው የሚውለው ግብአት በውጭ ምንዛሪ ከውጭ ሀገር ነው የሚገባው::

ግብአቱ ስላላቸውና የሙያው ባለቤት ለመሆን የሚፈልጉ እንዳሉም ነው ይሄ የሚያሳየው:: ተጠቃሚዎች በመኖራቸው ነው በግዥ ከውጭ እየገባ ያለው:: ቀልድ ይሁን እውነት አንድ ወቅት ላይ ከሴቶች አናት ላይ አርቲፊሻል ፀጉር ነቅለው የሚያመልጡ መስፋፋታቸው እየተነገረ ነበር:: ይህ ሁኔታ በስፋት ሲነገር የነበረው መንግሥት አርቲፊሻል ፀጉርን ጨምሮ ቅንጦት ለሆኑ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት እንደማይፈቅድ የወሰደውን እርምጃ ተከትሎ ነበር::

ምንም እንኳን እነዚህ አቅርቦቶች አያስፈልጉም የሚል ድምዳሜ ባይኖረኝም ግን ቅድሚያ የሚሰጠው ነው ብዬ አልወስደም:: ውበት ከውስጥ ነው ከሚሉ ወገኖች ነኝ:: ከላይ አምሮና ተውቦ ለመታየት የሚደረገው ጥረት ጊዜያዊ ነው:: የተሰራው ሜካፕ ሲጠፋ የሌሎችን እይታ የሚስብ ውበት አይኖረንም:: ይቀንሳል:: ሌላው በአርቲፊሻል እራስን ለማሳመር የሚደረገው ጥረት በራስ መተማመን ማሳጣቱ ነው::

በሜካፕ እራስዋን ማስዋብ የምታዘወትርና አርቲፊሻል ፀጉር የምትጠቀም ሴት የሜካፕ ጥገኛ ነው የምትሆነው:: የዚህ መዘዙ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ያለባትን ሀገር የበለጠ ችግር መፍጠር ብቻ ሳይሆን፣ ተጠቃሚውም የሚያገኘው ጥቅም ዘላቂ ባለመሆኑ ለስነልቦና ጉዳት መዳረጉ ነው::

ለመዋቢያ የሚውለው ግብአት ጥራት አስተማማኝነትም ጥያቄ ውስጥ የሚገባ በመሆኑ በቆዳ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት የማይሽር ጠባሳ ሊያሳርፍ ይችላል:: ‹‹ሲያጌጡ ይመላለጡ››የሚባለው አይነት እንዳይሆን መጠንቀቁ የተሻለ እንደሆነም ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል:: ስለዚህ ከላይ ለማማር ጥረት ከማድረግ ይልቅ ለውስጥ መጨነቁ የተሻለ ነው የሚል እምነት አለኝ::

ጤናማ የአመጋገብ ሥርዓትን መከተል ከተቻለ ውበት ይጠበቃል:: የጤና ችግር ሲያጋጥም ደግሞ ታክሞ ለበሽታው የሚሆን መድኃኒት ያስፈልጋል:: ይህን ሁሉ በማመዛዘን ቅድሚያ ሊሰጠው ለሚገባው ቅድሚያ መስጠት ከሁሉም የሚጠበቅ ተግባርና ኃላፊነት ነው::

ዜጎች በየትኛውም መልኩ በእጃቸው የገባውን ዶላር ሀገርና ሕዝብን በሚጠቅም ተግባር ላይ የማዋል የዜግነት ግዴታ እንዳለባቸው ይሰመኛል፣ በተለይም አሁን ላይ ሀገርና ሕዝብ በብዙ ችግሮች እየተፈተኑ ባለበት ሁኔታ ባለን አቅም ለወገኖቻችን ችግር መድረስ ይጠበቅብናል።

መንግሥትም አላስፈላጊ ለሆኑ ሸቀጦች ሊሰጥ ነበረውን የውጪ ምንዛሬ ከማቆም በተጨማሪ ፤የውጭ ምንዛሪው በየት በኩል ሾልኮ እየወጣ መሆኑን ማረጋገጥ፤ ቅድሚያ የማይሰጣቸው ሸቀጦች በየትኛውም ሁኔታ ወደ ሀገር ውስጥ በስፋት የማይገቡበትን መንገድ አግባብ ባለው መልኩ ተቆጣጥሮ ማስቆም ይጠበቅበታል::

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# አማራጭ የባሕር በር - የጋራ መልማት መሻት ነው

ግዛቸው ገ/ማሪያም

### ሰጥቶ ስለመቀበል እንደ መግቢያ

በበርካታ የዓለማችን ድንበር ተጋሪ ሀገራት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች የሀገራቱን ሕዝቦች የጋራ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ በሚያስችል በሥጥቶ መቀበል መርህን ሊመሩ እንደሚገባ፤ ይታመናል። ለዚህም የህንድና የቻይናን ተሞክሮ ለአብነት ማየቱ በቂ ነው።

ህንድ፣ ባንግላዴሽ፣ ቻይና እና ኔፓል ድንበር ተጋርተው የሚኖሩ ሀገራት ናቸው። ህንድ ከባንግላዴሽ በሰጥቶ መቀበል (give and take) መርህ፤ ቻይና ከኔፓል የሁለትዮሽ አሸናፊነትን መርሕ ባደረገ መንገድ (win win achieved by both sides) የሀገሮቻቸውን ጥቅም ማስከበር ችለዋል።

በሕዝብ ብዛት የዓለማችን ቁጥር አንድና ሁለት የሆኑት ቻይና እና ህንድም በተመሳሳይ መልኩ የሕዝቦቻቸውን እኩል ተጠቃሚነት ባደረገ መንገድ ችግሮቻቸውን ፈትተዋል። በድንበሮች አካባቢ ያሉ ሕዝቦች ታሪካዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብሮች ሕዝቦቹን ከመለያየት ይልቅ የበለጠ ተቀራርበው እንዲኖሩ አስችለዋቸዋል።

ሮዢንግ ጉዎ «Cross-Border Resource Management» በተሰኘው መጽሐፉ ሦስተኛ ዕትም ላይ፤ ሁለት ድንበር ተጋሪ ሀገራት በመካከላቸው በድንበር ዙሪያ የሚፈጠሩ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ቀድመው መሬት ላይ ያለውን እውነታ በማጤን እና የሕዝቦቻቸውን የጋራ ፍላጎት በመመልከት የሰጥቶ መቀበል መርህን ሊተገብሩ እንደሚገባ ገልጿል።

ይህ ሊሆን የሚገባው ወደፊት በሁኔታዎችወይምበጊዜሂደትሁኔታዎች መልካቸውን ቀይረው አለመግባባት ቢፈጠር እና ወደ ግጭት ቢገባ፤ ሁለቱ ድንበር ተጋሪ ሀገራት ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር መላው ሕዝቦቻቸውን ማስተባበር ስለሚኖርባቸው፤ ከወዲሁ የሕዝቦቻቸውን ይሁንታ ለማረጋገጥ የሕዝቦቻቸውን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ስለሚያስፈልጋቸው ነው።

የሰጥቶ መቀበል መርህ ውጤታማ እንዲሆን ችግሮችን ከነመፍትሄዎቻቸው ሊያካትት በሚችል ፓኬጅ ሊቀረጽ ይገባል። የሀገራቱን የሕዝቦች እና መንግሥታት ታሪካዊ ዳራ ከአሁናዊ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አነጻጽሮ፤ በድንበሮቹ አካባቢ የሚገኙ ሀብቶችን ያለ ምንም አድልኦ የሀገራቱን ሕዝቦች በጋራ ተጠቃሚ ማድረጉም ትኩረት ተሰጥቶት ሊታይ የሚገባ ነው።

### የወደብ ጉዳይ ወቅታዊነት

ኢትዮጵያ ከኤርትራ፤ ኬንያ፤ ሶማሊያ ወዘተ ጋር በንግድ ላይ በተመሠረተ የጋራ ስምምነት አማራጭ፣ የባሕር መዳረሻ በሮች የመጠየቅም ሆነ የማግኘት መብት እንዳላት ይታመናል። በተለይ የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝቦች ድንበርና የውሃ አካላት ከመጋራት ባለፈ የሁለቱ ሀገራት ሕዝቦች ሥነ-ልቦናዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና በሰው ልጆች መካከል ለዘመናት አብሮ በመኖር በሚገለፁ፣ በሚታዩና በማይታዩ ረቂቅ መስተጋብሮች የተቆራኙ ናቸው።

> **የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እያደገ በሄደ ቁጥር እና የወጣቱም ሆነ የሌላው የህብረተሰብ ክፍል ፍላጎትና የወጪ ገቢ ንግዱ የዚያኑ ያህል ስለሚጨምር ተጨማሪ አማራጭ የባሕር በር የግድ ያስፈልገናል**

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት መባቻ ጀምሮ ጣሊያን አውሮፓ ውስጥ የገጠማትን መሸነፍ ተከትሎ በሞግዚትነት ይዛ የቆየችውን ኤርትራን ለቃ መውጣቷን ተከትሎ ፤ንጉሡ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በሪፍረንደም እንድትዋሀድ ሰፊ ዲፕሎማሲያዊ ሥራዎችንም አከናውነዋል።

ይህንን ጠ/ሚ/ር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ በቅርቡ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲናገሩ «በንጉሡ ዘመን መጨረሻ አካባቢ የኢትዮጵያና የኤርትራ ጉዳይ በኮንፈዴሬሽን ነበር። ያኔ የነበረው መንግሥት ‹ኮንፈዴሬሽኑ አያስፈልግም፤ እኛ እንሻላለን፤ ጠንካራ ነን› ብሎ ፌዴሬሽኑን ቀደደው። የቀደደው መንግሥት ወድቆ የተቀደደበት ኃይል ደግሞ ‹የለም› ብሎ ታግሎ ዘመናት ከፈጀ በኋላ ኤርትራ ሀገር ሆነች። ይህ የትናንትናው ማታወሻችን ነው» ብለዋል።

ታሪክ ደግሞ ብዙ ያስተምረናል። በሰጥቶ መቀበል መርህ ለጋራ ጥቅም እንጂ በማንም ላይ የተለየ ኃይል የመጠቀም ፍላጎት በኢትዮጵያ በኩል እንደሌለ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ደጋግመው አረጋግጠዋል።

ላለፉት 30 ዓመታት ገደማ የባህር መዳረሻ በር ጉዳይ ጨርሶ አለመነሳት ብቻ ሳይሆን ከሁሉም አዕምሮ እንዲጠፋ ለማድረግ ተሞክሯል። ኢትዮጵያ ከዚያ በፊት 47 ሚሊዮን ሕዝብ ይዛ አጠቃላይ ምርቷም ከ12 ቢሊዮን ዶላር ባልዘለለበት ጊዜ በቢዝነስ ሕግ ተስማምታ፣ ሁለት የወደብ አማራጮችን (አሰብንና ጅቡቲን) ትጠቀም ነበር። በ1990 ዓ.ም በሁለት ታሪካዊ ቁርኝት ባላቸው ሀገራት መካከል ጦርነት ተቀስቅሶ ለሁለት ዓመት ሲዘልቅና በመጨረሻ ጦርነቱ በስምምነትና በእርቅ ሲቋጭ አሰብ ወደብ ቀርቶ በጅቡቲ ላይ ብቻ መንጠልጠሉ ግድ ሆነ።

አሁን ኢትዮጵያ የሕዝብ ቁጥሯ ከ120 ሚሊዮን ሕዝብ ዘልሎ ከአፍሪካ በሁለተኛነት አስቀምጧታል። የወጪ ገቢ ንግዷም ከ20 ዓመታት ወዲህ ብቻ ከሃያ እጥፍ በላይ አድጓል። አጠቃላይ ምርቷም ከ160 ቢሊዮን ዶላር በላይ እያደገች ያለችን ሀገር ይዞ የብዙ ሀገራት ዐይን ያረፈበትን የጅቡቲን ወደብ ብቻ እየተጠቀሙ መሰንበቱ እንዴት ያዋጣል? ጉዳዩ አጠቃላይ ለቀጣናው ሕዝቦች የጋራ ጥቅም የሚበጅና በተለይም ቀጣዩ ሀገር ተረካቢው ትውልድ ወጣቱ እፎይ የሚልበት በመሆኑ ሊተባበርና ለተግባራዊነቱ ከመንግሥት ጎን ሊቆም ይገባል።

የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እያደገ በሄደ ቁጥር እና የወጣቱም ሆነ የሌላው የህብረተሰብ ክፍል ፍላጎትና የወጪ ገቢ ንግዱ የዚያኑ ያህል ስለሚጨምር ተጨማሪ አማራጭ የባሕር በር የግድ ያስፈልገናል። የቀይ ባህርም ሆነ የሶማሌላንድ፣ የሶማሊያም ሆነ የኬንያ አማራጮችን አማትሮ ከወዲሁ በጋርዮሽ ጥቅም ላይ በመመስረት መፍትሄ ማበጀቱ ነገ ሳይሆን ዛሬ ማለቅ አለበት። በሰጥቶ መቀበል መርህ ጎረቤት ሀገሮችም የሚጎድላቸውን እንዲሞሉ የእኛ ትብብር የሚያሻቸው ሲሆን በእኛም በኩል የሚጎድለንን እነሱ ጋር ካለው እንድናሟላ በማድረግ በጋራ መጠቃቀም የሚቻልበት ወቅት አሁን ይመስለኛል።

በየክልሎች የሚገነቡት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ከሀገር ውስጥ ፍላጎት ባለፈ በዋናነት የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት ላይ ታስቦ በመሆኑ ተጨማሪ የባሕር መዳረሻ በር የዚያኑ ያህል የሚያስፈልገን ይሆናል። ወደሀገር ውስጥ የምናስገባቸውም ሆነ ከሀገር የምናስወጣቸው ሸቀጦች የምጣኔ ሀብት እድገታችን በጨመረ ቁጥር እነሱም በመጨመራቸው አንድ በንግድ ሕግ ስምምነት ላይ ተመስርተን የምንጠቀመው የጅቡቲ ወደብ ብቻውን ተሸክሞ ያዛልቀናል ብሎ ማሰቡ ጨርሶ የማይሆን ነው።

የዓለማችን ያደጉ ሀገራት አንዴም ከዐይናቸው እንዲርቅ በማይፈልጉት በዚሁ የጅቡቲ ወደብ ላይ ለአካባቢው ጂኦ ፖለቲካል ጥቅም ሲባል የጦር ካምፕ መሥርተው የተቀመጡበትን ወደብ እኛ ገና በእድገት ጉዞ ላይ ያለን ሕዝቦች የሆነ ኮሽታ ቢፈጠር እንኳን ጉሮሯችን እንደታነቀ ልንቆጥር ይገባል። ነዳጁ፣ ማዳበሪያው፣ መድኃኒቱ፣ መለዋወጫ እቃው ... በየት አልፎ ይግባ? የእኛስ ቡናው፣ ቆዳው፣ ቅመማ ቅመሙ፣ የግብርና ውጤቱ፣ ... በየት በኩል ይውጣ?

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ «እኛን የሚያስደነግጠን ምንድነው? አንድ ወደብ ነው ያለን። የጅቡቲ ሕዝብና መንግሥት ወንድማችን ነው። ግን ትላልቆቹ ቢጣሉ ጅቡቲ ላይ ካምፕ ስላላቸው ድንገት ቢታኮሱ የኛ ቦቴዎች ነዳጅ ሊያስገቡ አይችሉም። የጅቡቲ መንግሥት እየፈቀደ እኛም ፍላጎት እያለን በሌሎች ግጭት ምክንያት ለአንድ ሳምንት ነዳጅ ባይኖር አስቡት? ማዳበሪያ ካልገባ አስቡት? ...» ብለዋል።

ጉዳዩን ማሰብ ብቻ ሳይሆን ጉዳዩ ማናችንንም ሳይመርጥና ሳይለይ የእያንዳዳችንን ቤት በማንኳኳት መላ ሕይወታችንን በማመሰቃቀል የሳምንታት እድሜ እንኳን እንዳይኖረን ከማድረግም አልፎ ወደ ሌላም ሊያመራ ስለሚችል ጉዳዩ የሁላችንንም ትብብር እና ድጋፍ የሚጠይቅ፤ በጋራ እና በአንድነት መቆምን የሚሻ የህልውና እና የሰላም ጉዳይ ነው።

### አማራጭ የባሕር በር ባናገኝ ምን ሊፈጠር ይችላል?

የኛ ሕዝብ ቁጥርና የኢኮኖሚ እድገታችን ከገቢ ወጪ ንግዳችን ጋር ተያይዞ ወጥቶ የትየለሌ በሆነበት በዚህ ጊዜ በአንድ መተንፈሻ ብቻ የ120 ሚሊዮንን ሕዝብ ጉሮሮ ሞልቶ ማሳደሩ የመከበዱን ያህል የ 160 ቢሊዮን ዶላር የምጣኔ ግስጋሴንም እንዳለ ማስቀጠሉ እየከበደ ይሄዳል። ይህ ራሱን ለዘመናት እየኖረ ካለበት ድህነትና ኋላቀርነት ለማላቀቅ ከህልም ባለፈ ሌት ከቀን እየተጋ ለሚገኝ ሕዝብ ምን ማለት ሊሆን ይችላል?

### እንደ መውጫ

የሀገራችን የአማራጭ የወደብ ጥያቄ ለቀጣናው ሀገራት ካለው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አንጻር በአግባቡ ሊጤን የሚገባ ጉዳይ ነው። ሰጥቶ በመቀበል የጋራ ተጠቃሚነት መርህ ተግባራዊ መሆን ከቻለ ለአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች የጋራ ተጠቃሚነት አንድ ትልቅ አማራጭ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ክልሉን ማስተሳሰር የሚያስችሉ ዲጅታል አሠራሮችን ለማስፋፋት

ወርቅነሽ ደምሰው

ዲጅታል ኢትዮጵያን እውን በማድረግ ረገድ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው፤ ይህን ተከትሎም ለውጦችም እየተመዘገቡ ይገኛሉ:: ለዚህም የመብራትና የመሳሰሉት የአገልግሎቶች፣ የነዳጅ ግዥ ፣ የግብር ክፍያዎች በዲጂታል ቴክኖሎጂ እየተፈጸሙ ያሉበትን ሁኔታ በማሳያነት መጥቀስ ይቻላል::

ይህን ዲጂታል ቴክኖሎጂ የበለጠ ለማስፋፋት ኢትዮ-ቴሌኮም በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል:: ድርጅቱ ከበርካታ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር የዲጅታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ስምምነቶች በማድረግ አሠራሮቻቸው ዲጅታል እንዲሆኑ የሚያስችሉ በርካታ ሥራዎች እየሠራ ነው::




**ዘመናዊ የሸገር ከተማን በመገንባት/ሸገር ስማርት ሲቲ/ በኩል የተጀመሩ ሥራዎች አሉ፤ የሸገር ሲቲ ራሱን የቻለ የስትራቴጂ ዶክመንት ተዘጋጅቶለታል፡፡ ከተማው 12 ክፍለ ከተሞች፣ 36 ወረዳዎች እና 40 ቢሮዎች ያሉት ሲሆን፤ የዘመናዊ ከተማ/ የስማርት ሲቲ/ ፕሮጀክቱን በከተማው ለመጀመሪያ ጊዜ የማስተሳሰር ሥራ እየተሠራ ነው፡፡**

በቅርቡም ከኦሮሚያ ክልል ጋር የአገልግሎት አሰጣጥን የሚያዘምኑና የዘመናዊ ከተማ /የስማርት ሲቲ/ ትግበራን እውን የሚያደርጉ ዲጂታል መሠረተ ልማቶችን ለማቅረብ የሚያስችል ስምምነት አድርጓል:: በስምምነቱ ላይ የተገኙት በምክትል ፕሬዚዳንት ማዕረግ የኦሮሚያ ክልል የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ መስከረም ደበበ ክልሉ ማህበራዊና ተቋማዊ አገልግሎቶችን በስፋት እንደሚሰጥ ጠቅሰው፣ የመንግሥት አሠራሮችን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዙ እንዲሆኑ ከማድረግ አንጻር የያዘውን እቅድ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ለማሳካት እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል::

የቢሮ ሃላፊዋ እንዳሉት፤ ቀደም ሲል የመንግሥት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት አገልግሎታቸውን ለማዘመን ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በተናጠል ብዙ ሥራዎች ሠርተዋል:: ከእነዚህም ስምምነቶች አንዱ ድርጅቱ ከኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ ጋር የክፍያ ሥርዓትን ለማዘመን ያካሄደው ስምምነት ይጠቀሳል፤ በዚህ ስምምነት መሠረት የተሰሩ ተግባራትም ውጤታማ ናቸው::

በሌሎችም ዘርፎች የተጀመሩ ሥራዎች እንዳሉ የቢሮ ሃላፊዋ ጠቅሰው፣ እነዚህም በአሠራር ሥርዓት ውጤት አምጥተዋል ብለዋል:: የክልሉ መንግሥት አሁንም ማንኛውም የቴክኖሎጂና አገልግሎት የማዘመን ጥያቄ እንደ ክልል ለመመለስ የሚያስችል ስምምነት ከኢትዮቴሌኮም ጋር ማድረጉን አመላክተዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ መንግሥት አገልግሎት ሰጪ እንደመሆኑ መጠን አገልግሎት አሰጣጡ ውጤታማ እንዲሆን ቀልጣፋ፣ ጊዜ ቆጣቢና ግልጽ በሆነ መንገድ መስጠት ይጠበቅበታል፤ ዜጎች ይህንን አገልግሎት የሚጠይቁ በመሆኑ መንግሥት ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል፤ ይህንን ከማድረግ አንጻር የክልሉ መንግሥት ከክልል ፕሬዚዳንት ጽህፈት ቤት ጀምሮ እስከ ቀበሌ ያሉ የመንግሥት መዋቅሮችን በመረጃ አያያዝና ልውውጥ ያለባቸውን ክፍተት ለማሟላት የሚያስችል በቴክኖሎጂ የታገዝ አሠራር እንዲኖር ይፈልጋል::

ክልሉ በተለይም የትምህርት፣ የጤና፣ የቱሪዝምና መሰል አገልግሎቶች ተደራሽነትን ለማረጋገጥ እየሠራ መሆኑን ገልጸው፤ በዚህም ዘመኑ የደረሰባቸውን የቴክኖሎጂ አሠራሮች በማስረጽ ምርትና ምርታማነትን ማጎልበት ዋነኛው ሥራው ነው ሲሉ አስታውቀዋል::

የኢትዮ-ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፍሬሕይወት ታምሩ በበኩላቸው እንዳሉት፤ ተቋሙ የቴሌኮም መሠረተ ልማቶችን ተደራሽ ከማድረግ ባለፈ የተቋማትን የዲጂታል አገልግሎቶች ማስፋት ላይ በትኩረት መሥራቱን አጠናክሮ ቀጥሏል። ይህም ለዲጂታል ኢትዮጵያ እውን መሆን ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረክታል:: ከክልሉ ጋር የተፈረመው ስምምነትም በክልሉ እየተከናወኑ ያሉ የልማት ሥራዎችን በማፋጠን ዘመናዊነትን ለማረጋገጥ ያስችላል:: በዚህ ስምምነት ከሚከናወኑት መካከልም በዲጂታላይዜሽን ተቋማትን በማስተሳሰር የትምህርት ተደራሽነት፣ የማዕድን ሀብት ልየታና ምርትና ምርታማነትን ማዘመን እንዲሁም የግብርና ሥራን በቴክኖሎጂ የመደገፍ ሥራዎች ዋነኞቹ ናቸው ብለዋል።

በተጨማሪም የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎቶች፣ የጤና፣ የመሬት አስተዳደርና የዘመናዊ ቴክኖሎጂ /ስማርት ሲቲ/ ግንባታንም እንዲሁ በቴክኖሎጂ ማዘመን የስምምነቱ አካል ናቸው ሲሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ ገልጸዋል ።

ስምምነቱ የክልሉን ሀብት በተገቢው መልኩ ጥቅም ላይ ለማዋል በእጅጉ የሚያግዝና የዜጎችን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚያቃልል እንደሆነም የጠቆሙት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ በስምምነቱ መሠረት ሥራዎችን ለማከናወን ኢትዮ-ቴሌኮም በቁርጠኝነት እንደሚሠራም አረጋግጠዋል።

የኢትዮ ቴሌኮም የኔትወርክ መሠረተ ልማት ስትራቴጂና ኦፕሬሽን ፕሮጀክቶች የማኔጅመንት ኦፊስ ዳይሬክተር አቶ ዮሐንስ ጌታሁን ኢትዮ-ቴሌኮም በቀጣይ ከኦሮሚያ ክልልና ከሸገር ከተማ አስተዳደር ጋር የሚኖሩትን ሥራዎች አስመልክቶ በሰጡት ሰፊ ማብራሪያ ድርጅቱ ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ጋር እያከናወናቸው የሚገኙ ሥራዎች እንዳሉ ሆነው ሌሎች ተጨማሪ ሥራዎች እንደሚሠሩ አስታውቀዋል::

እሳቸው እንደሚሉት ፤ ክልሉ 20 የሚሆኑ ዞኖችና 180 የሚሆኑ ወረዳዎች እንዲሁም 30 የሚሆኑ ከተሞች አሉት፤ በርካታ የቱሪዝም መዳረሻዎችም ያሉት ክልል ነው:: ይህ ሁሉ ከቴክኖሎጂ አንጻር ሲታይ በዚህ ውስጥ ያሉትን አምራቾችን፣ ኢንዱስትሪዎችን፣ የመንግሥት ተቋማትን እና ማህበረሰቡን መጀመሪያ ማሰብ ያስፈልጋል:: እነዚህንም በመለየት ዘመናዊ በሆኑ የቴክኖሎጂ አማራጮች በኔትወርክ እርስ በርስ በማስተሳሰር በኔትወርክ የተሳሰሩ ዞኖች፣ ከተማዎች እና ወረዳዎች መፍጠር ያስፈልጋል::

ክልሉ ሰፊ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በቴክኖሎጂ ተናብቦ መሥራት ካልቻለ የሚፈለገውን አገልግሎትም ሆነ ሌሎች ሥራዎችን ለማከናወን አዳጋች ይሆንበታል፤ ይህም ክልሉን ለአላስፈላጊ ወጪም ይዳርጋል ያሉት ዳይሬክተሩ፣ የክልሉን ዞኖች፣ ከተሞች እና ወረዳዎችን በኔትወርክ ማስተሳሰር ከፍተኛ ወጪ መቀነስ ያስችላል፤ የሥራ ቅልጥፍናን ይጨምራል፤ ውሳኔ አሰጣጥን ያቀላል፣ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ያስችላል ሲሉ አብራርተዋል::

እሳቸው እንደገለጹት፤ በኔትወርክ የተገናኙ ቢሮዎችን ለመፍጠር እና ለማገናኘት የሚያስችሉ የሶፍትዌር እና የሀርድ ዌር ቴክኖሎጂዎች በስፋት እየተዘጋጁ ናቸው:: የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመን ፣አገልግሎት የሚሰጥባቸው ተቋማት አገልግሎቶችን በመለየት ማዘመን የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ::

እሳቸው እንዳሉት፤ ሌላው በኦሮሚያ ክልል ዘመናዊ የትራፊክ ማኔጅመንት ሲስተም ለመተግበር የሚያስችለውና በቀላሉ እየተሠራበት ያለው ሁሉንም ከተሞች የማገናኘት ሥራ ነው:: አሁን ላይ በብዙ ከተሞች የቪዲዮ ካሜራዎች እና የሰርቪላንስ ካሜራዎች እየተተከሉ ይገኛሉ:: ይህ ወደ ሥራ ሲገባ የመንገድ ደህንነት ስጋት ይቀንሳል፤ በዚህ በኩልም አሠራሩን በጣም ዘመናዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ::

በትምህርት ዘርፉም የኦሮሚያ ክልል ዘመናዊ የትምህርት ሲስተምን ለመዘርጋት የሚያስችሉ ፕሮጀክቶች እየተከናወኑ ይገኛሉ ሲሉ አቶ ዮሐንስ ጠቁመዋል:: እሳቸው እንዳሉት፤ በክልሉ 15ሺ 44 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና 556ሺ የሚሆኑ ተማሪዎች አሉ፤ እነዚህ ተማሪዎች በቴክኖሎጂ የተደገፈ ትምህርት እንዲያገኙ ለማድረግ ያለመ ተግባር ይከናወናል:: ይህም ውጤታማ ትምህርት ቤቶችን በመውሰድና ግብዓቶችን በመስጠት እንደሚጀመር ጠቁመው፤ ከዚያም ወደ ሌሎች እየሰፋ እንዲሄድ እንደሚደረግ አመላክተዋል::

በኢትዮ ቴሌኮም በኩል ዘመናዊ የትምህርት ሥርዓትን ለመዘርጋት የተደረገው ሙከራ ውጤታማ መሆኑን አቶ ዮሐንስ አስታውቀዋል፤ ይህ ሲስተም በተለያዩ ተቋማት አቅም ግንባታ ላይ እየተሰራበት መሆኑንም ጠቅሰው፣ በክልሉ ትምህርት ሥራ ላይ ለመተግበር ከክልሉ ጋር በትብብር እንደሚሠራ ገልጸዋል::

ከዚህ በተጨማሪም በክልሉ 30 ፖሊቴክኒክ ኮሌጆችና 323 የሚሆኑ ኮሌጅም ይገኛሉ ያሉት ዳይሬክተሩ፣ በእዚህ ደረጃም ዘመናዊ ትምህርት መስጠት የሚያስችል ሲስተም ለመዘርጋት እንደሚሠራ ይናገራሉ:: ይህም ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት እየተከናወነ ላለው ተግባር እንደሚረዳ አስረድተዋል::

ሀብትን አሟጦ ለመጠቀም በአይአርፒ (IRP) ሶሊሽን የፋይናንስ አሠራር የታገዘ አሠራር መዘርጋት በጣም ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ይቻላል የሚሉት አቶ ዮሐንስ ፤ የኢአርፒ አሠራርን መዘርጋት ተጀምረው የቀሩ ሥራዎች እንዳይኖሩ ማድረግ ያስችላል::

አንዳንድ የታሰቡ ሥራዎች ወደ ፈጻሚ (ውጤት) ሳይደርሱ የሚቀሩበት ምክንያት የኢአርፒ ሲስተም ካለመኖሩ የተነሳ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፣ የኢአርፒ ሶሊሽን ተግባራዊ ማድረግ በአጠቃላይ በክልሉ ፈጣን አገልግሎት መስጠት እንደሚያስችል አስታውቀዋል:: ከዚህም በተጨማሪ የፋይናንስ፣ የሰው ኃይል አስተዳደር እንዲሁም የክፍያ ሥርዓቶችን በማዘመን መሥራት እንደሚያስችል ጠቁመዋል::

የቴሌ ክላውድ ሶሉሽን መዘርጋት ሌላኛው ከክልሉ ጋር የሚሠራ ሥራ መሆኑንም ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል:: ከመረጃ አያያዝ ጋር ተያይዞ የሚነሳውን ችግር የሚያቀለው የቴሌ ክላውድ ሶሊሽን መሆኑን ጠቅሰው፤ ችግሩ ሁሉንም የክልል ተቋማት ሊመለከት የሚችል መሆኑንም ገልጸዋል:: ትምህርትን፣ ግብርናን፣ መሬትን እና የሰው ኃይልን የተመለከቱ በጣም ብዙ ዳታዎች እንዳሉ ጠቅሰው፣ እነዚህን በቴሌ ክላውድ ሶሊሽን ለማስቀመጥ እንደሚሠራ አመልክተዋል:: በዚህም በኩል ብዙ ወጪን መቀነስ እና ቴክኒካል እገዛን ማግኘት እንደሚቻል ጠቅሰው፤ የቴሌ ክላውድ ሶሉሽን አገልግሎት ክልሉን ለማዘመን ከሚሠራባቸው ጉዳዮች አንዱ እንደሆነ አስታውቀዋል::

ዓለም አቀፍ እውቅና ያገኘው የቴሌ ብር አገልግሎት በክልሉ የክፍያ ሥርዓቶችን ለማስፋፋት ጥቅም ላይ እንደሚውል አቶ ዮሐንስ ጠቅሰው፣ ቴሌ ብር በአሁኑ ወቅት በጣም በርካታ አገልግሎቶችን በተለያዩ ቋንቋዎች እየሠጠ እንደሚገኝ ተናግረዋል:: ኢትዮ-ቴሌኮም ካሉት 128ሺ ኤጀንቶች ውስጥ አብዛኛዎቹ የሚገኙት በኢሮሚያ ክልል መሆኑን ጠቅሰው፣ ከክፍያ ሥርዓት ጋር ተያይዞ በእያንዳንዱ የአርሶ አደር ኪስ ድረስ ዘልቆ መግባት የሚያስችል ሥራ እንደሚሠራ አመላክተዋል:: በዚህ የተነሳ የአግሪ ፋይናንስና ቴክኖሎጂ /ፊንቴክ/ አገልግሎት መስጠት እንደሚቻልም ጠቁመዋል::

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ ዘመናዊ ግብርና የሚጀመረው ዘመናዊ በሆነ የክፍያ ሥርዓት በመሆኑ መሠረታዊ የሆኑት የማዳበሪያ ስርጭት፣ የዘር እና የመሳሰሉትን አቅርቦቶች ጋር የተያያዙ ሥራዎችን ከቴሌ ብር የክፍያ ሥርዓት ጋር ለማያያዝ ይሠራል:: ሊበረታቱ የሚገባቸው እንደ ስንዴ ያሉ የማምረት ሥራዎችን ማስተዋወቅ እንዲሁም የገበያ ትስስር ማምጣት የሚቻልባቸው ሲስተሞችን መዘርጋትም ይቻላል:: የግብር ባለሙያ ድጋፍ መስጠት የሚችልባቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንደሚቻልም ጠቅሰው፤ ከምርት ሂደት ጋር የተያያዙ ስጋቶችን እና መረጃዎችንም እንዲሁ ለእያንዳንዱ አርሶ አደር ተደራሽ ማድረግ የሚቻልበትን ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችሉ ሥራዎችም ይሠራሉ ብለዋል::

ከክልሉ ጋር ለመሥራት የታሰቡ በርካታ ሶሉሽኖች መኖራቸውንም ዳይሬክተሩ ጠቁመው፤ አንዳንዶቹ የተዘጋጁ ሌሎቹ ደግሞ የክልሉን መሠረታዊ ችግሮች በመውሰድ ገና እንደሚሠሩ ጠቁመዋል::

ዘመናዊ የሸገር ከተማን በመገንባት/ሸገር ስማርት ሲቲ/ በኩል የተጀመሩ ሥራዎች እንዳሉም ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፤ የሸገር ሲቲ ራሱን የቻለ የስትራቴጂ ዶክመንት እንደተዘጋጀለትም ገልጸዋል:: የሸገር ከተማ 12 ክፍለ ከተሞች፣ 36 ወረዳዎች እና 40 ቢሮዎች ያሉት ሲሆን፤ የተጀመረውን የዘመናዊ ከተማ /የስማርት ሲቲ/ ፕሮጀክት ለመጀመሪያ ጊዜ የማስተሳሰር ሥራ እየተሠራ መሆኑን ይናገራሉ::

ሁሉንም ክፍለ ከተሞች እና ወረዳዎች በአንድ ላይ በማስተሳሰር ተጠሪ ቢሮዎችን ሳይቀር የሚያገናኝ የኔትወርክ መሠረተ ልማት ሥራ እንደሚሠራ ጠቅሰው፤ ሥራውን ለመጀመር የሚያስችለው ቅኝት /ሰርቬይ/ ማለቁንም አስታውቀዋል:: ከተሞች መግቢያ በር፣ ሕዝብ በሚሰበሰብባቸው ቦታዎችና ዋና ዋና ተቋማት በር ላይ ቪዲዮ ካሜራዎች መትከል ደህንነቱ የተጠበቀ ስማርት ሲቲ መገንባት ያስችላል ሲሉ አብራርተዋል::

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ዘመናዊ ከተማ /ስማርት ሲቲ/ ለመገንባት የኔትወርክ ዲዛይን ሥራው የተጠናቀቀ ሲሆን፣ በቀጣይ ወደ ትግበራ የሚገባ ይሆናል:: ይህም ተገልጋዩ የሚያነሳቸውን የኔትወርክ ፍጥነት ቅሬታዎችን በመቅረፍ ፍጥነት ያለው የኔትወርክ አገልግሎት እንዲያገኝ ማድረግ ያስችላል:: የሸገር ከተማ ዲጂታል ቢሮዎች የሚኖሩት ሲሆን፣ ይህም በየትኛውም ጊዜ፣ ቦታና በየትኛውም ዲቫይስ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ ያስችላል::

አሁን የሚገነባው ሸገርን ዘመናዊ ከተማ /የስማርት ሲቲ/ የማድረጉ ሥራ ነገ የሚመጡ የተለያዩ የከተማው አሠራሮችንም ማዘመን የሚችሉ ነገሮችን የሚያካትት ነው የሚሉት አቶ ዮሐንስ፣ ይህም ከተማዋ በዲጂታል በኩል የሚያስፈልጋትንና ማግኘት ያለባትን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በሙሉ ታሳቢ ያደረገ ነው ሲሉ አመላክተዋል::

# ወቅታዊ ትንታኔ

# ብዝሃነት፡- ፀጋ ወይስ ስጋት?

**ምሕረት ሞገስ**

የአንድ ሀገር ብዝሃነት በሃይማኖት እና በብሔር መጠን የሚገለፅ ነው፤ አንድ ሕዝብ በሃይማኖት የተለያየ የአምልኮ ሥርዓትን ሲከተል፣ ሕዝቡ የተለያየ ሃይማኖት አለው ይባላል። በተመሳሳይ መልኩ በአንድ ሀገር ሕዝብ ውስጥ የተለያየ ማህበረሰብ ሲኖር እና እነዚህ ማህበረሰቦች የየራሳቸው ባህል፣ ቋንቋ እና የአኗኗር ዘይቤ ሲኖራቸው ብሔር እንደሚባሉ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ብያኔዎች ያመለክታሉ። በዓለም ደረጃ በሀገራቸው ብዙ ብሔሮችን ከያዙ ሀገራት መካከል በቀዳሚነት ደረጃ ላይ የሚጠቀሱት ላይቤሪያ፣ ዑጋንዳ፣ ቶጎ፣ ደቡብ አፍሪካ ፣ ራሺያ እና ቤልጂየም የመሳሰሉት ናቸው።

ኢትዮጵያም ብዙ ብሔር እና የተለያየ ሃይማኖት ያለው ማህበረሰብ ካላቸው ብዝሃነትን እያስተናገዱ ከሚገኙ ሀገራት መካከል አንዷ ናት። ይህ የተለያየ ሃይማኖት ያለው ማህበረሰብ መኖሩ እና ብሔሮች መብዛታቸው ፀጋ ነው ወይስ ስጋት? ስንል ለምሁራን ባቀረብነው ጥያቄ ብዝሃነት ፀጋም ሆነ ስጋት የሚሆነው እንደተያዘበት መንገድ ነው ሲሉ ምላሽ ሰጥተውናል።

ፖለቲካ ሳይንስ እና ፌዴራሊዝምን ያጠኑት የፌዴራሊዝም አስተምሮት ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ሃይለየሱስ ታዬ (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፤ ብዝሃነት ለአንድ ሀገር ቀላል ጉዳይ አይደለም። ብዝሃነትን ማስተናገድ በጣም ትልቅ የፖለቲካ ዕውቀት እና አቅም የሚጠይቅ ነው። ብዝሃነት ሲኖር ከጀርባው ብዙ የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ሌሎችም ጥያቄዎች ይኖራሉ። አንዱ የፖለቲካ፣ ሌላው የኢኮኖሚ አንዱ ደግሞ የማህበራዊ ጥያቄ ሊኖረው ይችላል። ይህንን በደንብ ማስተናገድ እና ሀገራዊ አንድነት ላይም ሚዛኑን ጠብቆ መሄድ ካልተቻለ ብዝሃነት ስጋት ነው። ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ሚዛን ጠብቆ ማስተናገድ ከተቻለ ግን ፀጋ ይሆናል።

ብዝሃነትን በትክክል ያስተናገዱ ሀገሮች ጠንክረው ወጥተዋል። አስተካክለው ማስተዳደር ያቃታቸው አገሮች ደግሞ ብዝሃነት የግጭት ምንጭ ሆኖባቸዋል በማለት የዓለም ተሞክሮን በመጥቀስ በምሳሌ ሲያስረዱ፤ እንደማሳያ የድሮዎቹ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮች እስከ መፍረስ የደረሱት ብዝሃነትን በአግባቡ ባለማስተናገዳቸው ነው ብለዋል። ዩጎዝላቪያን መጥቀስ ይቻላል ካሉ በኋላ፤ በሌላ በኩል ብዝሃነትን በአግባቡ በማስተናገድ ውጤታማ የሆኑ ሀገሮችንም አንስተዋል። ሲውዘርላንድ ለብዙ ዓመታት የፌዴራል ሥርዓትን መሠረት በማድረግ ብዝሃነትን በማስተናገድ ጠንካራ ሆና መቀጠሏን አመላክተዋል። ካናዳ እና ፈረንሳይንም የጠቀሱ ሲሆን፤ ቤልጂየም እና ስፔንንም በማንሳት ብዝሃነት ቢኖራቸውም የተሳካላቸው መሆኑን ተናግረዋል።

ከኢትዮጵያ አንፃር ሲታይ፤ ቀደም ሲል በፊውዳል ዘመን አጠቃላይ ሕዝብን ከማየት ይልቅ ወደ ራስ ብሔር በማድላት፤ ሀገራዊ ጉዳዮች ይደረስባቸዋል በሚል የመተው ሁኔታ ነበር የሚሉት ሃይለየሱስ (ዶ/ር) በኢትዮጵያ የፌዴራል ሥርዓትን መተግበር ከተጀመረ ገና 30 ዓመታትን ብቻ ያስቆጠረ በመሆኑ፤ ጊዜው እንደሽግግር ጊዜ መታሰብ አለበት ብለዋል።

የሽግግር ጊዜ በመሆኑ እዚህ እና እዚያ ግጭቶች የሚታዩ መሆናቸውን በማመልከት፤ ነገር ግን ብሔር ብሔረሰቦች አኗኗራቸውን፣ ቋንቋቸውን እና ባህላቸውን ግልፅ በሆነ መልኩ የሚያሳዩበት መድረክ አግኝተዋል ብለዋል። በመንግሥት ደረጃ ዕውቅና አግኝተው ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር እየሞከሩ ነው። በዚህ ሂደት ሀገሪቷ ትፈርሳለች ተብሎ ቢሠጋም ግጭት ቢኖርም እስከ አሁን ኢትዮጵያ ሀገር ሆና ቀጥላለች ሲሉ ተናግረዋል።

‹‹የሽግግር ጊዜ መሆኑን ከማወቅ በተጨማሪ፤ ብዝሃነት ለኢትዮጵያውያን ተፈጥሯችን እና አብሮን የሚኖር በመሆኑ አምነን እንዴት አድርገን እናስተዳድረው በሚለው ላይ መነጋገር ይገባናል።›› ያሉት ሃይለየሱስ (ዶ/ር)፤ በኢትዮጵያ ለዚህ መልካም ሁኔታ መኖሩን አመላክተዋል። ኢትዮጵያውያን በጋብቻ እና በሌላ በሌላውም የተሳሰሩ መሆናቸው በምቹነት ሊታይ እንደሚገባ አስረድተዋል።

ነገር ግን ፖለቲካው ላይ ጫፍ እና ጫፍ ይዞ መካረር እንደሚስተዋል አስታውሰው፤ ይህ እንደ ኢትዮጵያ ላለች ሀገር እንደማይጠቅም አስረድተዋል። ፖለቲካው ከርሮ መጠፋፋት ላይ እንዳይደረስ የተማረው ማህበረሰብ ሀገርን እንዴት አድርጎ ዴሞክራሲ የሰፈነባት እና የበለፀገች ማድረግ እንደሚቻል ሊነጋገር ይገባል ብለዋል።

> **ለእያንዳንዱ ማህበረሰብ ክብር እና ዕውቅና ካልተሰጠ ስለኢኮኖሚ ልማት እና ስለሀገር እድገት መናገር አይቻልም**

አንዳንድ ሰዎች በሀገሪቱ ብዝሃነት መኖሩን እንደሚዘነጉ በመጠቆም፤ በተለይ በንግግር በኩል ሰዎች የሚናገሩት ነገር ሌላው ማህበረሰብ ላይ የሚፈጥረው ተፅዕኖ በደንብ መታሰብ አለበት ብለዋል። በንግግር ብቻ ሳይሆን በተለይ በተግባር መጠንቀቅም ይገባል ሲሉ አመልክተዋል።

ብዝሃነትን ለማስተናገድ በከፍተኛ ጥንቃቄና በብቃት መሥራት የግድ መሆኑን አስታውሰው፤ የኢኮኖሚ ችግርም ሁኔታውን የበለጠ ሊያወሳስበው ስለሚችል ኢኮኖሚው ላይም ሊታሰብ ይገባል የሚል ምክራቸውን ለግሰዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህሩ አቶ አሮን ደጎል በበኩላቸው እንደሚናገሩት፤ አንድ ዓይነት ነገር ያሰለቻል። አንድ ዓይነት ከመሆን ይልቅ ብዙ ዓይነት መሆን ያስደስታል። ስለዚህ ብዝሃነት ውበት እንጂ ስጋት መሆን የለበትም። የኢትዮጵያ ብዝሃነት በምንም መልኩ ለኢትዮጵያውያን ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች ስጋት ሆኖ አያውቅም። ስጋት ሊሆን አይገባም፤ እንደውም ዜጎች በውበትነት ሊቀበሉት የሚገባ ፀጋ ነው። እንደስጋት የሚታሰበው የአያያዝ ሁኔታው ነው።

‹‹ብዝሃነት የሚስተናገድበት መንገድ ሁሉንም አንድ ላይ በማምጣት ለኢትዮጵያ ዕድገት እና ለልማት የሚውልበትን መንገድ ካላወቅንበት እንደስጋት ሊታሰብ ይችላል። ብዝሃነቱ እውቅና አግኝቶ መብቶች ካልተከበሩ እና ሰዎች በእኩልነት ካልታዩ ስጋት ሊሆን እና ብዝሃነት የፀብ ምክንያት ሊሆን ይችላል።›› ብለዋል። እንደሃይለየሱስ (ዶ/ር) ሁሉ አቶ አሮንም፤ ብዝሃነት ያለባቸው ብዙ ሀገሮች አሉ። አውሮፓ ውስጥ እነቤልጂየም እነሲውዘርላንድ እና ሌሎችም የአውሮፓም ሀገሮች ብዝሃነትን የያዙበት እና ያስተዳደሩበት መንገድ በፀጋነት እንዲቀበሉት ያደረጋቸው መሆኑን አስረድተዋል።

ብዝሃነት የቱሪስት መስህብ መሆን አለመሆን ብቻ አይደለም። ብዝሃነት ብቻውን በርካታ ጥቅሞች አሉት። ብቻውን ስጋት መሆን አይችልም ያሉት አቶ አሮን፤ ነገር ግን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የሚቆጠረው እንደስጋት መሆኑን አብራርተዋል። ዋናው ነገር ስጋት ያደረገው የመሪዎች ችግር መሆኑን በመጠቆም፤ አሁን ድረስ ብዝሃነት ለመሪዎች እንደስጋት የሚታይ መሆኑን አብራርተዋል። ነገር ግን ከሕዝቦች አንፃር እንደውም ኢትዮጵያ በጣም መልካም ለሌሎች ምሳሌ መሆን የሚችል ባህል ያላት መሆኑን አስታውሰው፤ አብሮ መኖር፣ አብሮ መብላት፣ መተዛዘን እና መተሳሰብ የሚችል ሕዝብ ያላት ሀገር በመሆኗ ብዝሃነትን እንደስጋት ከማየት ይልቅ በፀጋነት መቀበሉ አዳጋች እንደማይሆን ተናግረዋል።

ሕዝቡ ጠንካራ የአብሮነት ባህል ስላለው ብዝሃነት ችግርም ሆነ ስጋትም አይሆንበትም። ያሉት አቶ አሮን፤ ነገር ግን መሪዎች በተለይ የአንበሳውን ድርሻ የሚወስዱት የፖለቲካ መሪዎች፣ የማህበረሰብ አንቂ ነን የሚሉ፤ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች እና የመንግሥት ባለሥልጣናት እና የሃይማኖት መሪዎችን ጨምሮ ሁሉም በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ማህበረሰብን የሚመሩ አካላት የሚፈጥሯቸው ችግሮች ብዝሃነት ስጋት እንዲሆን የራሳቸውን ሚና ይጫወታሉ ብለዋል። እነዚህ መሪዎች ሊያራምዷቸው የሚፈልጓቸውን የግል አመለካከቶቻቸውን ሕዝቡ ላይ ለመጫን ሲሞክሩ ብዝሃነትን በስጋትነት ይመለከቱታል ብለዋል። የፖለቲካ መሪዎች አመለካከታቸው ቢስተካከል እና አቃፊዎች ቢሆኑ፤ ፖለቲካው ቢስተካከል እና ቁርጠኝነት ቢታከል በትክክል ብዝሃነት ፀጋ መሆኑን ማረጋገጥ ይቻል እንደነበር አስረድተዋል።

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በሆነ ወቅት አንዱ ሌላውን የበታች የሚያደርግ አመለካከት ሊያሳይ ይችላል። ነገር ግን መሪዎች ይህንን ማስቆም አለባቸው ያሉት አቶ አሮን ለምሳሌ ዳግማዊ ምኒልክ አዋጅ አውጥተው እንደነበር አስታውሰዋል። አንድን ሰው ወይም ማህበረሰብ ለይቶ እንዲህ ነህ እንዲያ ነህ ማለትና በተለይም ሥራውን እና ሙያውን መሠረት አድርጎ ዕውቅና ሊያገኝበት የሚገባውን ልዩ ሙያ እና ክህሎት አናንቆ መጥራት እንደሚያስቀጣ አዋጅ አውጥተው እንደነበር እና ይህንንም በሰነድ ማረጋገጥ ይቻላል ብለዋል።

በፊውዳል ዘመን በነበረው ችግር የገዢው መደብ አካላት በወቅቱ የነበሩ ባላባቶች እና ገዢዎች ለአንዳንዱ ማህበረሰብ የሠጡት ስያሜ ነበር። ይሄ የተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን ብቻ ሳይሆን ስያሜ ያልተሰጠው ማህበረሰብ የለም። አማራውን፣ ትግሬውን ፣ ኦሮሞውን፣ ሃድያውን፣ ከንባታውን ለሁሉም ስያሜ ተሰጥቶት ነበር። ይህንን ስያሜ የሠጠው የፊውዳሉ አካል ሲሆን፤ ከዛ ወደ ማህበረሰቡ ወርዷል። ይህንን ለማስተካከል መሥራት ያለበት መንግሥት ነው። መንግሥት አሉታዊ ተፅዕኖ ሲኖር ሚናው መከልከል እና ሥርዓት ማስያዝ ነው። ይህን መሥራት ሲኖርበት ለጥፋቱ በዝምታ ካለፈው ዕውቅና ሰጥቷል ማለት ነው። ስለዚህ ብዝሃነት ፀጋ እንዲሆን መሪዎች ሚናቸውን መወጣት አለባቸው ሲሉ አሳስበዋል።

ሕዝብ የሚከተለው መሪውን ነው። መሪ የግድ ለሌሎች ምሳሌ እና አርአያ መሆን አለበት። መሪው ትክክለኛ ነገር ሲሠራ እና ስብዕና ሲኖረው፤ ለራሱ ክብር እና ሀገራዊ ራዕይ ሲኖረው ሕዝብም እንደዛው ይሆናል። በተቃራኒው መሪው በተሳሳተ መንገድ ሲሔድ ሕዝብም በተመሳሳይ መልኩ ይሔዳል። ብዝሃነት ስጋት እንዳይሆን መሪዎች ሀገራዊ ራዕይ ኖሯቸው ለሕዝብ ክብር መስጠት አለባቸው ብለዋል። መሪዎች ላደጉበት እና ለመጡበት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለእያንዳንዱ ሰው ክብር መስጠት እና መሥራት እንዳለባቸው አመላክተዋል።

ለእያንዳንዱ ማህበረሰብ ክብር እና ዕውቅና ካልተሰጠ ስለኢኮኖሚ ልማት እና ስለሀገር እድገት መናገር አይቻልም። መጀመሪያ ሕዝብ የሚለውን መስማት፣ ሕዝብን መታዘዝ እና ለአጠቃላይ ሕዝቡ መቆም ያስፈልጋል ብለዋል። ሌላው ትልቁ ነገር ኢትዮጵያን የመሰለች ብዝሃነት ያለባትን ሀገር ለመምራት የፖለቲካ ቁርጠኝነት እና አእምሮን ሰፋ አድርጎ ማዘጋጀት እንዲሁም ከብልሃት ጋር ቅንነት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል። እንደዚህ ካልሆነ የፈለገውን ያህል ዕውቀት እና ክህሎት፣ የበዛ ሀብት እና ፀጋ ቢኖርም ሀገርን ከችግር ማውጣት እንደማይቻልም ነው የተናገሩት።

ከዚህ በፊት የተፈፀሙትን ስህተቶች እየነቀሱ ወደ መድረክ በማምጣት ቁስልን ማከክ ወይም በሰው ቁስል ላይ እንጨት መስደድ ሳይሆን ያንን በይቅርታ ረስቶ አዲስ የሕይወት ምዕራፍ ለመጀመር መነሳት እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል። መሪዎች ቅንነት፣ ሰፊ ልቦና እና በዋናነት ደግሞ ያለምንም መድልዎ እና ልዩነት ለሕዝብ ክብር መስጠት እንዳለባቸው በማስታወስ፤ መሪዎች ራሳቸው ላለፈው ይቅርታ አድርገው እና ሕብረተሰቡም እርስ በእርሱ ይቅር እንዲባባል አመቻችተው መሪነታቸውን መቀጠል እንዳለባቸው አመላክተዋል።

ከኢትዮጵያውያን ብዝሃነት አንፃር አሁን በተያዘው መንገድ የሚቀጥል ከሆነ እና ካልተስተካከለ የወደፊቱ ያስፈራል የሚል እምነት እንዳላቸው ተናግረዋል። በየቦታው ከብሔር ጋር የተያያዙ ብዙ ችግሮች መኖራቸውን፤ በየቦታው ሰዎች የሚታፈኑ፤ የሚታገቱ እና የሚሞቱ መሆኑን በማስታወስ፤ ይሄ ሁሉ ሲካሄድ በየአካባቢው በየቦታው ያለው አስተዳዳሪ ምን እንደሚሠራ እስከ ፌዴራል ድረስ ችግሩን ለማስቀረት የተከናወነው በሙሉ መታወቅ አለበት ብለዋል።

የኢትዮጵያ መፃኢ ዕድል መልካም እንዲሆን እና አብሮ መኖር እንዲቻል በየደረጃው ሃላፊነት ያለባቸው መሥራት አለባቸው ብለዋል። በተቃራኒው ሚናቸውን ካልተወጡ እና እነርሱም የችግሩ አካል ከሆኑ እና ችግሩን ካስቀጠሉት የወደፊቱ ተስፋ ብሩህ አይሆንም ሲሉ ተናግረዋል።

አሁን ብሔራዊ የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሟል፤ እንደ ቀደመው የእርቀ ሰላም ኮሚሽን ወይም የድንበር እና የማንነት ኮሚሽን ተቋቁሞ የሰዎችን ጊዜ፣ የመንግሥትን በጀት ወስዶ የታለመለትን ዓላማ ከግብ ካላደረሰ ሁኔታው ከባድ እንደሚሆን አመልክተዋል። አሁንም ብሔራዊ ምክክሩ የተሳካ እንዲሆን መንግሥት ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል ብለዋል።

አቶ አሮን እንደገለፁት ሁሉ ሃይለየሱስ (ዶ/ር)ም እንደሚናገሩት፤ በእርግጥም ላለው ችግር ብዝሃነት ፀጋ እንዲሆን መሪዎች መሥራት አለባቸው። ነገር ግን ለብዙ ችግር እኩልነት መኖሩ መፍትሔ ቢሆንም እኩልነት በራሱ ብዙ ትርጉም እንዳለው መረሳት የለበትም። በሕዝብ ደረጃ ሁሉም እኩል ነው ቢባልም በኢኮኖሚ በኩል ሲታይ ለሁሉም እኩል ዕድል መስጠት የግድ መሆኑን ተናግረዋል። በዚህ ላይ የፌዴሬሽ ምክር ቤት በሚያስቀምጠው ቀመር መሠረት በጀት ይመደባል። ነገር ግን በአንድ ጊዜ የሁሉም ኢኮኖሚ እኩል ይሁን ማለት እንደማይቻል በመጠቆም፤ በዋናነት መፍትሔው ትብብር መሆኑን አስረድተዋል።

የኢትዮጵያ ችግር የፖለቲካ ሥርዓቱም በብሔር ላይ የተመሠረተ ነው። ዝቅተኛ ቁጥር ያለው ብሔር አለ። ብዝሃነት ፀጋ እንዲሆን ዝቅተኛ ቁጥር ያለውም መስተናገድ እና የሚሳተፍበት ሥርዓት መበጀት አለበት። ብዙ የአሠራር ሥርዓት እና ሕጎች እንዲሁም ፈፃሚ ተቋማት ያስፈልጋሉ። ሕግ አውጪውን እና አስፈፃሚውን የሚከታተሉ ተቋማት መኖር አለባቸው ብለዋል።

ሃይለየሱስ (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፤ ብዝሃነት ሲባል በፌዴራል ደረጃ ባለው ሥልጣን ላይ ብቻ ሳይሆን በቀጥታ በአገልግሎት አሰጣጥ ከሕዝቡ ጋር የሚገናኘው ቀበሌ ላይ መሠራት አለበት። ማንኛውም ነገር መነሻው ቀበሌ ላይ በመሆኑ የተማረ እና በአስተሳሰብ ማንም ይሁን ማን ማገልገል አለብኝ ብሎ የሚሠራ የተማረ ሰው እንዲሠራ መደረግ አለበት። እስከ አሁን ድረስ እንዴት ሔድን? ወደፊትስ እንዴት እንቀጥላለን ? በሚለው ላይ በጣም ሰፊ ውይይት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

አቶ አሮን በበኩላቸው፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥረት የሚያደርጉት መሪ ለመሆን ነው። ነገር ግን የሚመራ ሕዝብ ከሌለ መሪ መሆን አይቻልም። ስለምርጫ፣ ስለሥልጣንም ሆነ ስለሃይል መነጋገር የሚቻለው ሀገር ሲኖር ነው። ተቃዋሚ ፓርቲዎችም መጀመሪያ ሕዝቡ ጫና ሳይበረታበት በትክክል ኑሮውን እንዲኖር ሚናቸውን መወጣት አለባቸው። ሕዝብ ሲኖር ወደ ሥልጣን ጥያቄ ይገባሉ። ይህንን አርቀው ሊያስቡ ይገባል። ሥልጣናቸውን እና ኑሯቸውን ብቻ ሳይሆን የነገውን ሕዝብ ጉዳይ አርቀው ሊያስቡት ይገባል። ማህበረሰብ አንቂዎችም የሚያነቁት ሕዝብ እንዲኖር በሕዝብ ጉዳይ ላይ ማሰብ አለባቸው። የሃሰተኛ መረጃ እና የጥላቻ ንግግር አዋጅ ወጥቷል። የወጣበት ምክንያት እነዚህ አንቂ የተባሉ አካላት በሚያሰራጩዋቸው ሃሰተኛ መረጃዎች ሕዝብ አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ነው። ስለዚህ አዋጁን በትክክል መተግበር እና ለሕዝብ ማደር ከሁሉም ይጠበቃል።

እንደምሁራኑ ገለፃ፤ ብዝሃነት ስጋት አይደለም። ስጋት የሚሆነው ብዝሃነትን በተሳሳተ መንገድ ለማስተዳደር መሞከር ነው። ብዝሃነትን በአግባቡ ማስተናገድ ከተቻለ ከስጋትነት ይልቅ ፀጋ መሆን ይችላል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ሃያል ድምፆች - ለሴቶችና ሕጻናት ጾታዊ ጥቃት

መልካምሥራ አፈወርቅ

በርካቶች እንደሚስማሙበት ሴት ልጅ በአንዲት ውድ ሀገር ትመሰላለች:: ሀገር ማለት ቀለሟ ደማቅ፣ ትርጓሜዋ ብዙ ነው:: ምንጊዜም ለሁሉም መኖሪያና ምልክት ሆና ትሰየማለች :: ሁሌም የማንነት መለያ ናትና ትውልድን በዘመን ሚዛን እያሻገረች ትኖራለች::

ሴት ልጅ ማለትም እንደ ሀገር ሁሉ የትውልድ ዐሻራ ናት:: እናት፣ እህት ፣ ልጅና ሚስት ነችና ለማንነት መሠረትና መድረሻ ሆና ትዘልቃለች::

በአንድ ቃል ተወስኖ በብዙ የሚተረጎመውን ‹‹ሴት›› ይሉትን ታላቅነት አክብሮ የያዘ ቢኖር አንዳች አይከስርም :: እናቱን የሚወድ፣ ሚስቱን የሚያከብር፣ እህቱን የሚጠብቅ ፣ ልጁን የሚያሳድግ ሁሉ መቼውንም ከህልውናው እውነታ ፈቀቅ አይልምና::

ተደጋግሞ እንደሚባለው ‹‹ሴትን ልጅ ማስተማር ሀገርን እንደማስተማር ይቆጠራል›› ሴት ቁምነገረኛነቷ፣ ብልሀትና ዘዴዋ ከራሷ አልፎ ለሀገርና ወገን ካስማ ሆኖ ይቆማል :: ሴት ልጁን በወጉ ያሳደገ ፣ በትኩረት ያስተማረ ቤተሰብ ለዛሬው ድካሙ ነገን በእጥፍ ይከፈለዋል:: ከምንም በላይ ግን ሴት ልጅ ከጥቃትና በደል ስትጠበቅ ፍሬዋ ያምራል ፣ ዓላማዋ ይሳካል :: ይህ ይሆን ዘንድም የወንዶች አጋርነት በተግባር ዕውን ሊሆን ግድ ይላል::

እንደ አሮፓውያኑ ዘመን አቆጣጠር በ1991 በካናዳ ‹‹ሞቲሪያል ›› ከተማ የሚገኙ ሴቶች የዘመኑን ፆታዊ ጥቃትን በማውገዝ ፣ ድርጊቱን የሚቃወም እንቅስቃሴ ማካሄድ ጀመሩ:: ወቅቱ የሴትን ልጅ ጥቃት ለመከላከል ይቻል ዘንድ ድምጾች ከፍ ብለው የሚሰሙበት ነበር ::

በሞንቲሪያል ከሚገኝ አንድ ኮሌጅ እንቅስቃሴውን ያካሂዱ የነበሩ በርካታ ሴቶች የብዙሃን ዓይንና ጆሮ በመሆን ትኩረትን ሳቡ:: ዓላማቸውን የተረዱ ወገኖችም ከጎናቸው ቆመው ቃላቸውን አስተጋቡ:: ‹‹የሴቶች መብት ይከበር ፣ ጥቃት ይቁም›› ይሉት ሃሳብ ያልተዋጠለት አንድ ግለሰብ ግን ውስጡ ከሌሎች ተለየ:: ይህን መልዕክት አምርሮ ጠላው፣ ተጠየፈው ::

የሰውየው ስሜት በጥላቻ ብቻ አልቆመም:: ያነገተውን መሣሪያ እንዳጠበቀ ወደ ኮሌጁ ቅጥር ጥሶ ገባ :: ታጣቂው ጥይቱን አቀባብሎ መተኮስ ሲጀምር አፍታ አልቆየም:: ዒላማው በሰዎች ፣ በተለይም በሴቶች ላይ ነበር::

በዕለቱ የሴቶች ጥቃትን ሲያወግዙ ከነበሩት መካከል 14 ሴቶች በታጣቂው ጥይት ሕይወታቸውን ተነጠቁ:: ይህ አሳዛኝና አስደንጋጭ ድርጊት ግን የጥቂት በጎ አሳቢ ወንዶችን ስሜት ነካ :: የጥይት ሠለባ የሆኑትን እህቶቻቸውን ዓላማ አድምቆም ከሕይወት ነጣቂው ድርጊት በተቃራኒ ለመቆም አስቻላቸው::

እነዚህ ወንዶች የሴቶቹን ድንቅ ዓላማ አልዘነጉም:: ድርጊቱን ከመቃወም ባለፈ በወንዶች የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለማስቆም የሚያስችለውን የነጭ ሪቫን ዘመቻን ማካሄድ ጀመሩ :: ወንዶቹ ለሴቶች አጋርነታቸውን በገሀድ ያሳዩበት ይህ ዘመቻ ተጠናክሮ መቀጣጠሉ በመላው ዓለም ተጽዕኖ ማሳደሩ አልቀረም::

እ.ኤ.አ ህዳር 16 ቀን በ1999 በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በተወሰነው መሠረት የነጭ ሪቫን ቀን በመላው ዓለም ዕውን እንዲሆን ተደረገ:: በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ማንኛውንም ጥቃት ለመከላከል የወንዶች አጋርነት የሚታይበት ይህ ጊዜ ዛሬ ላይ አስራስድስቱን ቀናት ለፀረ- ፆታዊ ጥቃት ትኩረት በመስጠት ይንቀሳቀሳል::

ከህዳርዳር 16 እስከ ታህሳስ 1 በሚኖሩት አስራ ስድስት ቀናት ሀገራችንን ጨምሮ በመላው ዓለም የጸረ - ፆታ ጥቃት የንቅናቄ ዘመቻ ይካሄዳል:: በነዚህ ቀናት የሚኖሩ እንቅስቃሴዎች ዋንኛ ትኩረት ወንዶች በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጾታዊ ጥቃቶችን የመከላከል አጋርነታቸውን ለማሳየት ነው:: ይህ ዕውን እንዲሆንም ነጭ ሪቫን በደረታቸው ላይ በማኖር አለኝታነታቸውን ይገልጻሉ::

ዘንድሮ ይህ ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ32ኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ18ኛ ጊዜ ተከብሯል:: በሀገራችን የተከበረው ይህ የፀረ- ፆታ ጥቃት ዘመቻ

‹‹መቼም፣ የትም፣ በምንም ሁኔታ ፆታዊ ጥቃትን ዝም አልልም›› የሚል መሪ ቃልን የያዘ ነው :: የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከኦሮሚያ ሴቶችና ሕጻናት ቢሮ ጋር በመተባበር ህዳር 21 ቀን 2016 ዓ.ም በአዳማ ከተማ ባካሄደው የጸረ ፆታ ጥቃት ቀን ለዕለቱ የተለየ




ትኩረት በመስጠት በርካታ ሃሳቦች ተነስተውበታል::

በኃይሌ ሪዞርት በተዘጋጀው በዚሁ የንቅናቄ መድረክ በክብር እንግድነት የተገኙት የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ክብርት ሳህለወርቅ ዘውዴ በዝግጅቱ ለታደሙት ተሳታፊዎች ዕለቱን አስመልክተው መልዕክት አስተላልፈዋል:: ፕሬዚዳንቷ እንደገለጹት አሳሳቢ ለሆነው የሴቶች ጥቃት ትኩረት በመስጠት ዘንድሮ በሀገራችን የተከበረው የንቅናቄ ዘመቻ አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው::

‹‹መቼም፣ የትም፣ በምንም ሁኔታ ፆታዊ ጥቃትን ዝም አልልም ›› በሚል መርህ መከበሩም እስከዛሬ በሴቶች ጉዳይ የነበረውን ዘመን ያስቆጠረ ዝምታ ለመስበር የሚያስችል ነው::

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉበዔ ሴቶችን አስመልክቶ በርካታ የሕግ ማዕቀፎችን አጽድቋል:: ፕሬዚዳንቷ እንደሚሉት የሴቶች የእኩልነት ጥያቄ ያላለቀና ለዘመናት ይዘነው የምንጓዘው ጉዳይ ነው:: በታሰበው ልክ ችግሮች አለመፈታታቸው ግን ተገቢ ለውጦች አልመጡም:: ለዚህ እውነታ መፍትሄ ለመስጠትም ገና ብዙ መሥራት የሚያሻው ይሆናል:: ፆታን መሠረት አድርገው የሚፈጸሙ ጥቃቶች በሴቶች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ከፍ ያለ ነው::

ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ለታዳሚዎቹ ባስተላለፉት መልዕክት ይህን ጊዜ ስናከብር በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚታወቁት የአስራ ስድስት ቀናት የጸረ- ፆታ ጥቃት ላይ ብቻ ትኩረት አድርገን ሌሎች ጊዜያትን በመርሳት ሊሆን አይገባም:: እያንዳንዱ ሰው ምን ላድርግ ሲል የሚከውነው ተግባር ሌሎችን ከወደቁበት የሚያነሳ ሊሆን ያስፈልጋል::

‹‹ተገቢው የሕግ ማዕቀፍን ማውጣት ብቻ ሳይሆን ተገቢው ግንዛቤን ተጨባጭ የሚባል ተግባር ሊኖር ግድ ነው›› ያሉት ፕሬዚዳንቷ የሰላም ዕጦት በሚታይባቸውና በሥራ ቦታዎች ለሚስተዋለው የሴቶች ጥቃት የተለየ ትኩረት ማድረግ ግድ ይላል:: በዓይን የማይታዩና የማይዳሰሱ፣ ውስጥን የሚጎዱ ሥነልቦናዊ ጥቃቶችም በራስ መተማመነን ይነጥቃሉና ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል ብለዋል::

በእለቱ ሃሳባቸውን ለታዳሚዎች ያጋሩት የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር) በበኩላቸው ጾታዊ ጥቃትና ጎጂ የሚባሉ ልማዶች በሀገራችን የሚገኙ በርካታ ሴቶች በሁሉም ዘንድ በሚካሄዱ ሁለንተናዊ የልማት እንቅስቃሴ ላይ በንቃት እንዳይሳተፉ በማድረግ የድርሻቸውን እንዳይወጡ እንቅፋት ይሆናል::

ሚኒስትሯ እንደገለጹት ይህ ችግር ዕንቅፋት ከመሆኑ ባሻገር ሴቶች ከሚገኙ ቱርፋቶች ሁሉ ተቋዳሽ እንዳይሆኑ መሰናክል የሚሆን እኩይ ተግባር ነው::

ጾታዊ ጥቃት የነገ ሀገር ተረካቢ የሆኑ ሕጻናት የመጪውን ተስፋና ዕድላቸውን በማጨለም የልማት ቅበብሎሹ ከትወልድ ወደ ትውልድ በተሳካ ሁኔታ እንዳይሻገር የሚያደርግ በመሆኑ ሁሉም ሊያወግዘውና ሊቃወመው ይገባል::

የአስራስድስቱ ቀናት የጸረ- ጾታዊ ጥቃት እንቅስቃሴ በነጭ ሪቫን መለያ የሚታወቅ ነው:: ሚኒስትሯ እንዳሉትም በዋንኛነት ወንድ አጋሮች በእህቶችና ሕጻናት ላይ ጥቃት እንዳይደርስ ቃላቸውን የሚያድሱበት፣ ቃል የሚገቡበትና ተግባራዊ ምላሽ የሚሰጡበት የንቅናቄ ዘመቻ ይሆናል::

ፆታዊ ጥቃት በሴቶችና ሕጻናት ላይ በደረሰ ጊዜ ጉዳቱ አካላዊ ብቻ አይሆንም:: ጉዳቱ የከፋ ሥነልቦናዊ ስብራት አለው:: የጤና ችግሮችን ጨምሮም ውስብስብ ለሚባሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች አጋልጦ ይሰጣል:: ከድርጊቱ መከሰት በኋላ በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ የሚኖረው የተዛባ አመለካከት ችግሩን ለማባባስ የሚኖረውን ድርሻ ላቅ ያለ ያደርገዋል::

ሚኒስትሯ እንዳስገነዘቡትም ይህን መሰሉን የማይበጅ እሳቤ በማስወገድ ከተጎጂዎች ጎን መቆም ከሁሉም የማህበረሰብ ክፍል የሚጠበቅ የሃላፊነት ድርሻ ይሆናል::

በዚህ ረገድ የኢፌዴሪ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲሁም የኢትዮጵያ መንግሥት ጾታዊ ጥቃት ከግለሰብ አንስቶ በሀገርና በማህበረሰብ ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ከግምት ውስጥ ያስገባል:: ከዚህም ተያይዞ ለሴቶችና ሕጻናት ሠብዓዊ መብት መከበር ጉልህ አስተዋጽኦ ያላቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ከማጽደቅ ባሻገር ለማሠራት ዕንቅፋት የሆኑ ሕጎችን በማሻሻል አዳዲስ የአሠራርና የአደረጃጀት ለውጦች ላይ ትኩረት ያደርጋል::

እንደሚኒስትሯ ገለጻ የተቋማትን አቅም በማጠናከር የተቀረጹ የሕግ ማዕቀፎችን በሥራ ላይ እንዲውሉና ስኬታማ እንዲሆኑ ጠንካራ ሕጋዊና አስተዳደራዊ ርምጃዎች ሲወሰዱ ቆይተዋል::

የሚኒስቴር መሥሪያቤቱ በሴቶችና ሕጻናት ላይ ዕድሜና ጾታን መሠረት አድርገው የሚፈጸሙ ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶችን ለመከላከል ግብረሃይል መቋቋሙን የገለጹት ሚኒስትሯ የአስፈጻሚ አካላትን አቅም በሥልጠና ለማጎልበትም ጥረቱ እንደሚቀጥል ተናግረዋል::

የአስራስድስቱን ቀናት የንቅናቄ ዘመቻ በማክበር እለቱን አስበውና አክበረው በጉባዔው መሀል ለተገኙ ወንዶች በሙሉ ክብርት ሚኒስትሯ ምስጋናቸው አቅርበዋል:: ዕለቱን አስመልክተው የፍትህ ሚኒስቴርን በመወከል በስፍራው የተገኙት አርሚያስ የማነ ብርሃን (ዶ/ር) እንዳሉት በሴቶችና ሕጻናት ላይ የሚፈጸመውን ጥቃት ለመከላከል ለአስራስድስት ቀናት ብቻ ትኩረት መስጠት ተገቢ አይሆንም ::

በእሳቸው ዕምነት እንደጉዳዩ ክብደት ዓመቱን በሙሉ መንቀሳቀስና መሥራት አስፈላጊና ግዴታ ይሆናል:: የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ዘርፈ ብዙ እንደመሆኑ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሕግ ተቀርጾ ስትራቴጂ ተነድፎ ሊሠራበት ይገባል:: እንደ ኤርሚያስ (ዶ/ር) ገለጻ ጥቃቱን ከመከላከል ባሻገር ይህን ዓላማ ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል ስትራቴጂ ተነድፎ ተጠናቋል::

በብሄራዊ አስተባባሪ ኮሚቴ አማካኝነት የተነደፈውና በሁለት ዋና ዋና ዓላማዎች ላይ የተዋቀረው ሃሳብ መብትና ግዴታዎችን አካቶ የያዘ ነው:: የጉዳቱ ሰለባዎች ከሚደርስባቸው የጤና፣ የሥነልቦናና አካላዊ ጉዳቶች አኳያ መልሶ ለማቋቋም የበርካታ ተቋማትን የሃላፊነት ድርሻ የሚጠይቅ ይሆናል::

እነዚህንና መሰል ጥያቄዎችን ለመመለስ አስተባባሪ ኮሚቴ በ2001 ዓ.ም የተቋቋመ ሲሆን በውስጡም 19 ተቋማትን ያካተተና በፍትህ ሚኒስቴር አስተባባሪነት፣ በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰብሳቢነት የሚመራ ነው::

የመግባቢያ ስምምነቱ ስለመፈረሙ የገለጹት ኤርሚያስ (ዶ/ር) ሁሉንም የፍትህ ተቋማት ጨምሮ የተለያዩ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በአጋርነት የሚሳተፉበት ስትራቴጂ ስለመሆኑ ተናግረዋል::

ኤርሚያስ (ዶ/ር) 19 ኙም ተቋማት በተሰጣቸው የሥራ ድርሻ መሠረት ሃፊነታቸውን በወጣት ላይ እንደሚገኙ ይናገራሉ:: በሴቶችና ሕጻናት ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለመዋጋት፣ የፖሊሲ፣ የሕግ የአሠራርና ስትራቴጂ መስመሮችም ተዘርግተዋል::

አግባብነት ያላቸው ሕጎችና ፖሊሲዎች በሚመለከታቸው አካላት ተመርምረው ስለመጽደቃቸው የገለጹት ኤርሚያስ (ዶ/ር) እንዳስፈላጊነቱ የቴክኒክና የአማካሪ ኮሚቴዎች መዋቀራቸውን ጭምር አስታውቀዋል:: ተግባራዊ የሚባል የአምስት ዓመት ስትራቴጂ የተነደፈለት ይህ አደረጃጀት በአሁኑ ጊዜ ዕቅዱን አስገምግሞ ለማፀደቅ ችሏል::

ከዚህ ባሻገር ዓላማቸውን በሴቶችና ሕጻናት ፍትህና እንክብካቤ ላይ ያደረጉ ማዕከላት በአዲስ አበባና በክልሎች መቋቋማቸውን የገለጹ ሲሆን ጥቃቱን ለመከላከል የሚያስችል የብሔራዊ ስትራቴጂ ዕቅድ ተነድፎ ይፋ ለማድረግ የሚያስችል ፍጻሜ ላይ መድረሱን ገልጸዋል::

ከዚሁ ጎን ለጎን ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በመለየት አፈጻጸማቸውን ተግባራዊ የማድረግ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ መሆኑ ተጠቁሟል::

በመድረኩ ላይ እንደተነሳው የተነደፈውን የስትራቴጂ ዕቅድ የሚመለከታቸው አካላት ትኩረት ሊሰጡበት ይገባል:: ይህ የድርጊት መርሀግብር ሴቶችና ሕጻናት ከጥቃት ስጋት ነጻ የሚሆኑበትን ሁኔታ የሚያመቻች ነው:: በዚህ ሂደትም ለነዚህ ወገኖች የተቀናጀ አገልግሎት ተደራሽ ሚሆንበት አሠራር ተግባራዊ ይደረጋል::

ሴቶችና ሕጻናት በሚደርሳባቸው ጾታዊ ጥቃት ለሚያጋጥማቸው አካላዊና ሥነልቦናዊ ጉዳቶች ችግሮችን በተገቢው መንገድ መፍታት አስፈላጊና ተገቢ መሆኑን በስትራቴጂው ያረጋገጠው መርሀግብር አሠራሩን ወደ ትውልድ ላማሻገር አበክሮ ለመሥራት ተዘጋጅቷል::

ከ2016 ዓ.ም እስከ 2020 ዓ.ም ድረስ ተቀርጾ ተግባራዊ የሚደረገው ብሔራዊ ስትራቴጂ በሕግ አግባብ ጸድቆ ወደስራ ለመግባት ግዴታዎቹን ያጠናቀቀ ሲሆን ይህ ስትራቴጂም በዕለቱ በተዘጋጀው መድረክ ላይ ይፋ በመሆን በሕግ አግባብ ጸድቆ ለመመረቅ ችሏል:: በዕለቱ መርሀግብር ላይ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ክብርት ሳህለ ወርቅ ዘውዴን ጨምሮ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ሀደ ስንቄዎችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል::

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

አዲስ ዘመን ትናንት፤ ዛሬና ነገም ጭምር ነው። ታሪክና ክስተት ሁነትና አጋጣሚዎች ሁሉም ከአዲስ ዘመን ትናንቶች ይቀዳሉ። አዲስ ዘመን ድሮ ዛሬም የሚነግረን ይህንኑ ነው። 1960ዎቹ በተለይም 1966 የዛሬው ምንጫችን ግዙፍ ኩሬ ነው። ኢትዮጵያ የዓለም አቀፉ የፋኦ ምክር ቤት አባል የሆነችበትን የመጀመሪያው ዘገባ፤ የኢትዮጵያን ፊደላት ወደ አንድነት... የሐረር ጋሪዎች ሠልፍ አሳይተዋል። ጥቁሮችን በዕባብ? በዘረኝነት ናላው የዞረው ዲን ባርበር... እንዲሁም ከጳውሎስ ኞኞ ደብዳቤዎችም ታክለው ለዛሬው ትውስታ ተሠናድተዋል።

### ኢትዮጵያ የፋኦ ምክር ቤት አባል ሆነች

ኢትዮጵያ 27 አባሎች የሚገኙበት የተባበሩት መንግሥታት ምግብና የእርሻ ድርጅት(ፋኦ) ምክር ቤት አባል ሆና የተመረጠች መሆኗን ክቡር አቶ በለጠ ገብረጻድቅ የእርሻ ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር ኅዳር 29 ቀን በነበረው የጋዜጠኞች ጉባዔ ላይ አስታውቀዋል።

**(አዲስ ዘመን ኅዳር 30 ቀን 1966ዓ.ም)**

### የሐረር ጋሪዎች ሠልፍ አሳዩ

በሐረር ከተማ የሚገኙ ጋሪ ነጂዎች ከሐረር ማዘጋጃ ቤት በተሰጣቸው ምክር መሠረት በገንዘባቸው የተለየ የመታወቂያ ልብስ በማሰፋት መስከረም 12 ቀን 1966ዓ.ም ከቀትር በላይ ከነፈረስ ጋሪዎቻቸው ሰልፍ በመውጣት፤ የተሰጣቸውን ምክር በመፈጸም በጎ ተግባራቸውን አሳይተዋል።

**አዲስ ዘመን መስከረም 13 ቀን 1966ዓ.ም)**

### 233ቱ ፊደላት በ33 ብቻ ተቻቻሉ

233 የሆኑት የኢትዮጵያ ፊደላት፤ በ33 ብቻ ለመጻፍ የሚያስችል አዲስ የፊደል ቅርጽ ማውጫ ተሠርቶ ወጥቷል።

አዲሱን የፊደል ቅርጽ ማውጫ የሠሩት በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ በቁም ጽሕፈት ክፍል ውስጥ የሚሠሩት አቶ ኃይሉ ጌታሁን ናቸው።

**(አዲስ ዘመን ኅዳር 13 ቀን 1966ዓ.ም)**

### ሂሊኮፕተሩ ጠፍቶ ተገኘ

ጎንደር፡- በእርሻ ሚኒስቴር የአዝዕርትና የተክል ክፍል ንብረት የሆነው ሂሊኮፕተር ጥቅምት 4 ቀን 1966ዓ.ም ከቀኑ ሰባት ሰዓት ላይ የመቶ አለቃ ሽብሩ አያና የተባለው ፓይሌት ከአዲስ አበባ ወደ ጎንደር እየነዳ ሲሔድ የሞተሩ ዘይት ስለፈሰሰበት ተሰናክሎ በበጌምድር ሰሜን ጠቅላይ ግዛት ቋርሳ በተባለው ቀበሌ ወድቋል።

**አዲስ ዘመን ጥቅምት 7 ቀን 1966ዓ.ም)**

### ጥቁሮችን በዕባብ?

ከሲልማ፡- የአላባማ ፖሊስ ኃይል ባለፈው ሐሙስ አንድ ነጭ በአንድ ጥቁር አሜሪካዊ አፍ ውስጥ ነፍስ ያለው ዕባብ ለመክተት ሲታገል አግኝቶ በመያዝ እንዲታሠር ያደረገ መሆኑን ተገልጿል።

ጂምስ ክላርክ የተባለ አንድ የሲልማ ቀበሌ ሹም እንዳስረዳው ይህ 27 ዓመት የሆነው ዲን ባርበር የተባለው ወንጀለኛ ነጭ የብጥብጥ አስነሺ በመሆንና ድንገተኛ አደጋም በመጣል በተጨማሪ የተከሰሰ መሆኑን አስታውቋል።

የቀበሌውም ሹም ከዚህ በማያያዝ ሲያመለክት ተከሳሹ ዲን ባርበር ከዚህ ከፈጸመው ወንጀል ሌላ በሲልማ ቀበሌ በሚገኝ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የዘር ልዩነትን ለማስወገድ ስብሰባ በተደረገበት ዕለት አራት የሚሆኑ ጥቁር አሜሪካውያንን በዕባብ ያስነከሰ መሆኑን ደግሞ ገልጿል።

ይህም የቀበሌ ሹም ጉዳዩን በመዘርዘር አደጋ የደረሰባቸው ሰዎች የነከሳቸውን ዕባብ ለመበቀል በተነሱ ሰዓት ብጥብጥ ተደርጎ እንደነበር አስረድቷል

**(ሔ.ሴ.ፍ.ፒ)**

**(አዲስ ዘመን ታህሳስ 10 ቀን 1966ዓ.ም)**

### ጥያቄ አለኝ ይድረስ ለጳውሎስ ኞኞ

* ባለቤቴ አንድ የውጭ አገር ዜጋ ከቤታችን ጋብዞ አመጣና ከቤት የተቀመጠውን አበባ አይቶ አደነቀን። ግን ከዚያው ከሳሎን ሆነው ከባለቤቴ ጋር ሲያወሩ ፈረንጁ ሲጃራ እያጨሰ አመዱን ወይም ኩስታሪውን ከአበባው ማስቀመጫ ውስጥ ይጨምር ጀመረ። በዚህ አደራረጉ አልተናገርንም እንጂ ባለቤቴም እኔም በጣም ተናደናል። ፈረንጁ እንደሔደም አበባውን ከነአመዱ አውጥተን ጣልነው። ፈረንጁ አበባውን አድንቆ የሲጃራውን አመድ ከውስጡ መኮስተሩ እኛን ለመናቅ ነው? ወይስ ሌላ ምክንያት አለው?

### ወይዘሮ ጸ.ደ

ትልቁ ነገር እንደተናደዳችሁ ያለመናገራችሁ ነው። ፈረንጁ ያን ያደረገው አበባው ቶሎ እንዳይደርቅ ብሎ ምግብ መስጠቱ ነው እንጂ እናንተን ለመናቅ ወይም ለሌላ ጉዳይ ብሎ አይደለም። እሜትዬ! ለወደፊቱም እንግዶች ሲወጡሎት በሲጃራ መኮስተሪያ ላይ ያጠራቀሙትን አመድ እውጭ ከማፍሰስ በአበባ ማስቀመጫው ላይ ይጨምሩት። ግን እንዳይበዛ። ያበባውን ዕድሜ ያረዝመዋል። ለመሆኑ ምን አይነት አበባ ነው የሚወዱት?

**(አዲስ ዘመን ጥር 13 ቀን 1965ዓ.ም)**

* ከዚህ በፊት በሀገራችን ውስጥ የሕንድ ፊልም በብዛት ይታይ ነበር። አሁን እስከአንዱም ጠፍቷል። ለዚህ ምክንያቱ ምንድነው?

- መታየቱ ይታያል። በዚህ ላይ የምነግራችሁ ዳግመኛ ስለሕንድ ፊልም የምትጽፉልኝ ሰዎች እንዳትጽፉልኝ። ምክንያቱም በብዛት እየደረሱኝ እንደማያቸው ከመጠን በላይ የሚያሞግስና ሌላም ሌላም አድርጋችሁ ስለምትጽፉ እየታዘብኳችሁ ጥያቄያችሁን ጥዬዋለሁና ዳግመኛ እንዳትጽፉልኝ።

**(አዲስ ዘመን የካቲት 16ቀን 1964ዓ.ም)**

* አንድ የተፈረደበት ሰው ሊገረፍ በሚተኛበት ጊዜ ሰውየው ከመገረፉ በፊት መሬቲቱን ሁለት ጊዜ ገራፊው የሚገርፈው ለምንድነው?

### ወታደር ሞገስ እሸቱ (ከመቱ)

ድሮ አንድ አስተሳሰብ ነበር። አንድ ሰው በሚመታበት ወይም በሚገረፍበት ጊዜ ሰይጣን አብሮ ይመታል ወይም ይገረፋል ይባል ነበር። ስለዚህ ሰይጣኑ ቸኩሎ ሰውየውን ከጅራፍ ጋር ሊገርፈው ስለሚፈልግ፤ ሰይጣኑን ለማታለል መጀመሪያ መሬቷን ሲገርፍ ሰይጣኑም የሚገርፈው መጀመሪያ ስለሆነ የሰይጣኑ ምት ከመሬት ላይ እንዲያርፍ ብለው ነው። ለምሳሌ አንዱ አንዱን ሰው ዦሮ ግንዱን ሲያንጋጋው ዦሮው እንዳጋጣሚ ሊደነቁር ይችላል። ይህም የሚባለው ሰይጣኑ አብሮት ስለመታው ነውና ምነው መጀመሪያ ከሌላ ዘንድ በመታው ይባላል። የሚደፈነው ግን ከጥፊው ጋር ከዦሮው ውስጥ የሚገባው አየር የጆሮውን ከበሮ ስለሚቀድደው ነው።

**(አዲስ ዘመን ኅዳር 29 ቀን 1966ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ

## በሱዳን በርዳታ መኪኖች ላይ በተፈጸመ ጥቃት ሁለት ሰዎች ተገደሉ

በሱዳኗ መዲና ካርቱም በርዳታ መኪኖች ላይ "ሆን ተብሎ በተፈጸመ ጥቃት" ሁለት ሰዎች መገደላቸውን ዓለም አቀፉ ቀይ መስቀል አስታወቀ። በዚህ ጥቃት ከሟቾቹም በተጨማሪ ሰባት ሰዎችም መቁሰላቸው ተነግሯል። የርዳታ መኪኖቹ የቀይ መስቀል አርማ በግልጽ የያዙ መሆኑን ያስታወቀው ተቋሙ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰላማዊ ዜጎችንም ደህንነቱ ወደ ተጠበቀ ቦታ ለመውሰድ ያቀኑ የነበሩ ናቸው ተብሏል።

በጥቃቱ ከተጎዱትም መካከል ሶስቱ የረድዔት ድርጅቱ ሠራተኞች እንዳሉበትም ነው ዓለም አቀፉ ቀይ መስቀል የገለጸው። ጥቃቱንም "አስደንጋጭ እና ዘግናኝ" ሲል ነው ተቋሙ ባወጣው መግለጫ የፈረጀው። በሱዳን በጦሩ እና በፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ መካከል እየተካሄደ ያለው የርስ በርስ ጦርነት ስምንተኛ ወሩን ይዟል።

የሱዳንን መጻኢ ፈንታንም ለመቆጣጠር የሱዳን ጦር ኃይል መሪ አብደል ፈታህ አል ቡርሃን እና የፈጥኖ ደራሽ ኃይል (አርኤስኤፍ) መሪ ጄነራል መሃመድ ሃምዳን ዳጋሎ ወይም ሄምቲ ተፋጠዋል። በርካታ ተቋማት እና ሀገራት ግጭት የማቆም ስምምነት ላይ እንዲደረስ ያደረጉት ተደጋጋሚ ጥረት ፍሬ ባያፈራም ኢጋድ ተስፋ ሰጪ ጉዳይ አግኝቻለሁ ብሏል።

ሁለቱ ተፋላሚ ወገኖች የተኩስ አቁም ተግባራዊ ለማድረግ እንዲሁም ፊት ለፊት ለመነጋገር ቃላቸውን ሰጥተውኛል ብሏል። የሱዳን ጦር መሪ ጄነራል አብደል ፈታህ አል ቡርሃን እንዲሁም የፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ አዛዥ ጄነራል መሐመድ ሃምዳን ደጋሎ ለግጭቱ ሰላማዊ እልባት ለመስጠት ቁርጠኝነት አሳይተዋል ማለቱ ነው የተገለጸው።

ጥቃቱ የተፈጸመው እሁድ ዕለት በከተማዋ ምዕራብ በኩል በምትገኘው አል ሻጃራ ሰፈር መሆኑንም ቀይ መስቀል ገልጿል። የርዳታ መኪኖቹ "ከመቶ በላይ የሚሆኑ ተጋላጭ ሰላማዊ ዜጎችን" ከመዲናዋ ካርቱም ወደ ዋድ ማዳኒ ለመውሰድም የተዘጋጁ ናቸው ተብሏል።

ዜጎቹን የማስወጣት ዘመቻው ከተፋላሚ ወገኖች ጥያቄ እንዲሁም ትብብር ጋር የሚፈጸም እንደሆነ ያስታወቀው ተቋሙ ሁለቱም ወገኖች የደህንነት ዋስትና ሰጥተው ነበር ብሏል። የዓለም አቀፉ ቀይ መስቀል የሱዳን ተልዕኮ ኃላፊ ፒየር ዶርብስ ጥቃቱን "ተቀባይነት የሌለው" ነው ብለዋል።

"የቀይ መስቀል አርማን እያዩ ክብር አለማሳየታቸው አስደንጋጭ ነው። በዓለም አቀፉ ሠብዓዊ ሕግ መሠረት ሊከበር እንዲሁም ሊጠበቅ ይገባዋል" ሲሉም ነው



ያሳሰቡት። "የዚህ ተልዕኮ ዋነኛ ዓላማ እነዚህን ሰላማዊ ዜጎች ደህንነቱ ወደተጠበቀ ቦታ መውሰድ ነበር ነገር ግን በአሳዛኝ ሁኔታ የንጹኃን ሕይወት ተቀጥፏል። በዚህ ጥቃት ቤተሰቦቻቸው ለተገደሉባቸው ሰዎች ጥልቅ ኀዘኔን እየገለጽኩ የተጎዱትም ቶሎ እንዲያገግሙ እመኛለሁ" ሲሉ ገልጸዋል።

ቀይ መስቀል ደህንነቱ ወደተጠበቀ ቦታ ሊወስዳቸው ያሰባቸው ህሙማን፣ ህጻናት፣ ወላጆቻቸውን ያጡ ታዳጊዎች እና በዕድሜ የገፉ ዜጎችን ነው። እነዚህን ዜጎች የማስወጣት ይህ ተልዕኮ የተሰረዘ ሲሆን የጸጥታው ሁኔታም እንደገና እስኪገመገም ድረስ ይቆያል መባሉን ቢቢሲ ዘግቧል።


## ሩሲያ የጉዞ እገዳ የተጣለባቸው ዜጎች ፓስፖርታቸውን እንዲያስረክቡ የሚያስገድድ ሕግ አወጣች

ሩሲያ የጉዞ እገዳ የተጣለባቸው ዜጎች ፖስፖርታቸውን እንዲያስረክቡ የሚያስገድድ ሕግ አወጣች። በሀገሪቱ የወጣው አዳስ ሕግ ወደ ውጭ እንዳይጓዙ እግድ የተጣለባቸው ሩሲያውያን በተነገራቸው በአምስት ቀናት ውስጥ ፓስፖርታቸውን ለመንግሥት ያስረክባሉ።

በዚህ ሕግ መሠረት የሩሲያ ባለሥልጣናት በወታደሮች፣ በፌደራል የደህንነት ሠራተኞች፣ በወንጀለኞች እና የመንግሥት ሚስጥር በሚያውቁ ወይም የተለየ ጠቀሜታ ያለው መረጃ ባላቸው ሰዎች ላይ የጉዞ እገዳ መጣል ይችላሉ። ከዜጎች የተመለሰው ፓስፖርት እገዳውን በጣለው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም በሀገር ውስጥ ደህንነት ይቀመጣል።

እንደሕጉ ከሆነ እገዳው ከተነሳ በኋላ የፖስፖርቱ ባለቤት ማመልከቻውን እንዲጠናቀቀ ይመለስለታል። በወታደራዊ ወይም በሌላ የሲቪል ሥራ ላይ ያሉ እና ጊዜያዊ እግድ የተጣለባቸው ዜጎች እገዳው ሲነሳ ፓስፖርታቸውን ለመውሰድ፣ የተሰጣቸው የአገልግሎት ጊዜ ማለቁን የሚያሳይ መረጃ ይዘው መቅረብ እንደሚጠበቅባቸው ሕጉ ጠቅሷል።

ሮይተርስ ፋይናንሻል ታይምስ ባለፈው ሚያዚያ ላይ ያቀረበውን ሪፖርት ጠቅሶ እንደዘገው የሩሲያ የደህንነት መሥሪያ ቤት የከፍተኛ ባለሥልጣናት እና የመንግሥት ኩባንያዎች ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፓስፖርቶችን ወርሰዋል ሲል አል ዐይን ዘግቧል።



# ስፖርት

## ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደው ዲጂታል የቼስ ውድድር ተጠናቀቀ

**ዓለማየሁ ግዛው**

ባለፉት ቀናት ሲካሄድ የቆየው 4ኛው ‹‹ፍሊንት ስቶን ሆምስ ለሁሉም ክፍት የሆነ እና የግል የበላይነትን የማስጠበቅ የቼስ ውድድር›› ከትናንት በስቲያ ፍጻሜውን አግኝቷል፡፡ ውድድሩ ከፍተኛ ፉክክር ማስተናገዱም ተጠቁማል፡፡ ውድድሩ ከዓለም የቼስ ፌዴሬሽን በድጋፍ መልክ በተገኘ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ በመታገዝ ‹‹ብሊቲዝና ራፒድ›› የተሰኙ የቼስ ጨዋታዎችን በማካተት በቀጥታ ስርጭት መካሄዱም ተገልጿል፡፡

ለሁሉም ክፍት የሆነ የግል የበላይነት የማስጠበቅ የቼስ ቻምፒዮናው ከህዳር 28 ጀምሮ ለተከታታይ ሶስት ቀናት በልደታ መርካቶ አዳራሽ በርካታ የቼስ ተወዳዳሪዎችን ያፋለመ ሲሆን፣ የውድድሩ አሸናፊዎችም ተለይተዋል፡፡ የኢትዮጵያ ቼስ ፌዴሬሽን ከዓለም አቀፉ የቼስ ፌዴሬሽን በድጋፍ ባገኘው የኤሌክትሮኒክስ ቼስ ቦርድ ( Digtal live chess) በመታገዝ የተካሄደ ሲሆን ከፍተኛ ፉክክር ማስተናገዱ ተገልጿል፡፡

ፌዴሬሽኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባው ዲጂታል የቼስ ቦርድ የዳኞች ጫናን ከመቀነስ በተጨማሪ ከዳኝነት ጋር ተያይዞ የሚነሱ ቅሬታዎችን የሚያስቀር መሆኑ ተጠቁማል፡፡ በተጨማሪም ውድድሩን በቀጥታ በማህበራዊ ድረ-ገጽ በሚለቀቅ ማስፈንጠሪያ አማካኝነት ለተመልካች እንደቀረበ ታውቀል፡፡

ውድድሩ በዓለም አቀፉ የቼስ ፌዴሬሽን እውቅና የተሰጠውና ልምድ ያላቸው እና ወጣቶች የተሳተፉበት በመሆኑ የተወዳዳሪዎቹን ወቅታዊ ብቃትና ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉ እንዲሁም አዳዲስ ተወዳዳሪዎች እድል እንዲያገኙ ታስቦ እንደተካሄደ የኢትዮጵያ ቼስ ፌዴሬሽን አስታውቋል፡፡ በፍሊንት ስቶን ሆምስ የተሰየመው ይህ ውድድር የፌዴሬሽኑን ዓመታዊ ውድድሮች የተለያዩ ድርጅቶችና ተቋማት እንዲደግፉ በር ከፋች መሆኑም ተገልጿል፡፡ በዚህም ውድድር ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ከ70 በላይ ተሳታፊዎች የተመዘገቡ ቢሆንም ከ50 በላይ ተወዳዳሪዎች ብቻ መሳተፋቸው ተጠቅሷል፡፡



ሃምሳ ተወዳዳሪዎች በውድድሩ ተፎካካሪ ሆነዋል፤

ቼስ የተለያዩ የውድድር ዓይነቶችን ያካትታል፤ እነዚህም የሚለያዩት በሰዓት አማካኝነት ሲሆን ክላሲካል፣ ብሊቲዝና ራፒድ የቼስ ጨዋታዎች ይጠቀሳሉ፡፡ ክላሲካል የሚባለው የቼስ ጨዋታ ለእያንዳንዱ ተጫዋች አንድ ሰዓት ተኩል የሚሰጠው ሲሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያለው የተጫዋቾች ብቃት የሚለካበትና ደረጃ የሚውጣበት ውድድር ከሆነ 30 ሰከንድ ጭማሪ ይኖረዋል፡፡

በዚህ ውድድር ብሊቲዝና ራፒድ የቼስ ጨዋታ በዓለም አቀፉ የቼዝ ፌዴሬሽን የተመዘገቡ ውድድሮች ሲሆኑ ለእያንዳንዱ ተጫዋች የሚሰጠው ሰዓት ይለያያል፡፡ ለራፒድ የቼስ ጨዋታ 15 ደቂቃ ከተሰጠ በኋላ 10 ሰከንድ ጭማሪ ይኖረዋል፡፡ ብሊቲዝ የሚባለው ደግሞ በጣም ፈጣን እና ለእያንዳንዱ ተጫዋች 5 ደቂቃ የሚሰጠው ሲሆን የ3 ሰከንዶች ጭማሪ የሚደረግም ይሆናል፡፡

ውድድሮቹን በ5፣ 7 እና በ9 ዙሮች ማካሄድ የሚቻል ቢሆንም የተሻለ ፍክክር እንዲኖርና ጠንካራ ተወዳዳሪዎችን ለመለየት በእያንዳዱ 9 ዙሮችን የፈጀ ፍልሚያ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት በ9 ዙሮች ተወዳድሮ ጠንካራ ፍልሚያን በማከሄድ በድምር ውጤት አብላጫ ነጥብን ያስመዘገቡ ተወዳዳሪዎች የሜዳሊያና የገንዘብ ተሸላሚ መሆን ችለዋል፡፡

በዚህም መሰረት ከፍተኛ የማሰብና የማሰላሰል ብቃትን በሚጠይቀው ውድድር በራፒድ ወንዶች ፉክክር ደሳለኝ ፍቀዱ፣ ያለምዘውድ መኮንን እና ዮሴፍ ክፍሌ የወርቅ፣ ብርና የነሐስ ሜዳለያ ተሸለሚ መሆን ችለዋል፡፡ በሴቶች ራፒድ ሊያና አመህ፣ ሙላካ ፈቲ እና ወርዳ ፈቲ የተባሉ ተወዳዳሪዎች በተመሳሳይ ከ1-3ኛ በመውጣት ተሸልመዋል፡፡

በብሊቲዝ ወንዶች ውድድር በተደረገው ፉክክር ሚልኪ አብዲሳ፣ አዲስዓለም ተመስገን እና አቤል ሰይፉ የወርቅ፣ የብርና የነሐስ ሜዳለያን ሲሸለሙ፣ በብሊቲዝ ሴቶች ፉክክር ሙለካ ፈቲ፣ ሊያና አመህ እና ወርዳ ፈቲ ከአንድ እስከ ሶስት ያለውን ደረጃ በመያዝ ተሸላሚ ሆነዋል፡፡ ከሜዳለያ በተጨማሪ የገንዘብ ሽልማት የተበረከተ ሲሆን፤ በድምር ውጤት 1ኛ የወጣው ዮሴፍ ክፍሌ የ15 ሺ ብር ተሸላሚ መሆን ችሏል፡፡ ሶስት ተወዳዳሪዎች እኩል ውጤት በማስመዝገባቸው የ12 ሺ ብር ተሸላሚ ሆነዋል፡፡

የኢትዮጵያ ቼስ ፌዴሬሽን ባለሙያ የዝና ሙኔ፣ ፌዴሬሽኑ በርካታ ውድድሮችን እንደሚያከናውን አስታውሰው የግል የባላይነትን የማስጠበቅ ውድድር ለ4 ጊዜ እንደተካሄደ ተናግረዋል፡፡ የዘንድሮውን የግል የበላይነትን የማስጠበቅ ውድድርን ለየት የሚያደርገው ስያሜ ከማግኘቱና ዓለም አቀፍ እውቅና የተሰጠው ከመሆኑ በተጨማሪ በዲጂታል ቼስ ቦርድ መታገዙ እንደሆነም ገልፀዋል፡፡ ይህም ቴክኖሎጂ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ለውድድር ጥቅም ላይ እንደዋለ አስረድተዋል፡፡ ፍሊንት ስቶን ሆምስ ፌዴሬሽኑን ለረጅም ዓመታት እየደገፈ እንደቆየና ለዚህም ውድድር ሙሉ ወጪውን ሸፍኖ የውድድሩን ስያሜ እንደወሰደም አክለዋል፡፡ ይህንን አርአያ አድርገው ሌሎች ድርጅቶችም ዓመታዊ የፌዴሬሽኑን ቻምፒዮናዎች እንዲደግፉ በር ይከፍታልም ብለዋል፡፡